# አዲስ ዘመን

እፕድ

ማክሰኞ

82ኛ ዓመት ቁጥር 115 ታኅሣሥ 25 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!


# ኢትዮጵያ

## ከጎረቤት አገሮች ጋር ሁለገብ ትብብርን ለማጠናከር የመሰረተ ልማት ትስስሮችን እያሳደገች ነው



**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ከጎረቤት አገሮች ጋር ያላትን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ትብብሮችን ለማጠናከር የመሰረተ ልማት ትስስሮችን እያሳደገች መሆኑን በሱዳን የኢትዮጵያ ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደር ይበልጣል አእምሮ ገለጹ፡፡

አምባሳደር ይበልጣል በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ የአፍሪካ ሕብረት መስራችና የሕብረቱ መቀመጫ አገር በመሆኗ ለአፍሪካውያን ነጻነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጋለች፡፡ በአፍካውያን አንድነት የምታምን፣ የአፍሪካውያንን ችግር በአፍሪካውያን መፈታት አለበት የሚል ጽኑ እምነት ያላት በመሆኑ ለአፍሪካውያን ችግር በአፍሪካውያን መፍትሔ እንዲመጣ እየሰራች ትገኛለች ብለዋል፡፡

አምባሳደሩ እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ ከጎረቤት አገሮች ጋር ያላትን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ትብብር በማጠናከርና የመሰረተ ልማት ትስስሮችን እያጎለበተች ነው፡፡ የአገራችንን ነባራዊ ተጨባጭ ሁኔታ በአግባቡ በመረዳት

ኢትዮጵያ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ውሉና አዳራቸውን ጎዳና ላይ ያደረጉ ከ16 ሺህ በላይ ዜጎችን ለማቋቋም እየተሠራ ነው

## * ከ9 ሺህ በላይ የሚሆኑት ማገገሚያ ማዕከል ገብተዋል

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- በተያዘው ዓመት ከ16 ሺህ በላይ ውሎና አዳራቸውን ጎዳና ያደረጉ ዜጎችን ለማቋቋም እየተሠራ ነው ሲሉ የአዲስ አበባ ሴቶችና ህፃናት ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ አስታወቀ፡፡

የአዲስ አበባ ሴቶችና ህፃናት ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ የማህበራዊ ሴፍቲኔት የኑሮ ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ቢኒያም ግርማ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ከፌዴራል መንግሥት በተያዘ መደበኛ በጀትና ከዓለም ባንክ በተገኘ ብድር ውሎ እና አዳራቸውን ጎዳና ላይ ያደረጉ ዜጎችን ለማቋቋም እየተሠራ ነው፡፡

ቢሮው ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ በተደራጀ መልኩ ዜጎችን ከጎዳና የማንሳትና ወደ ማህበረሰቡ የመቀላቀል ሥራዎች ሲሠራ መቆየቱን የጠቀሱት አቶ ቢኒያም፤ ዜጎቹን መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በማቀናጀትም መሥራት የሚችሉትን ወደ ስራ መስክ እያሰማራ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡ በተመሳሳይ በተያዘው ዓመት ከ16 ሺህ በላይ ውሎና አዳራቸውን ጎዳና ያደረጉ ዜጎች ይቋቋማሉ ብለዋል፡፡

ዳይሬክተሩ እንዳሉት፤ ውሎና አዳራቸውን በመዲናዋ ጎዳና ላይ ያደረጉ ዜጎችን ወደ ተቋቋሙ ማዕከላት በማስገባት የሥነልቦና እና የምክር አገልግሎት እንዲያገኙ በማድረግና የተለያዩ አጫጭር የሙያ ሥልጠናዎችን በመስጠት የማቋቋም ስራ እየተሠራ ነው።

ባለፉት አምስት ወራት ሊሠራ ከታሠበው ከ16 ሺህ በላይ ውሎና አዳራቸውን ጎዳና ካደረጉ ዜጎች ከ9 ሺህ በላይ ዜጎች አቃቂ ቃሊቲ በሚገኘው ጊዜያዊ ማገገሚያ ማዕከል እንዲጠለሉ በማድረግ የተለያዩ ድጋፎች

ውሉና ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል





ፎቶ - ሃይሽ አብርሃ

# የማትሪክ ውጤት ማጣትን በ37 A+ የተበቀለው ወጣት

**ዳግማዊት ግርማ**

ግርማ ዳባ ይባላል፤ የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ የጤና ኮሌጅ የ2014 የዋንጫ ተሸላሚ ተመራቂ ነው። ግርማ ዛሬን ለማየት የሄደው ርቀት ቀላል አልነበረም። በሕይወት ጉዞው ላይ ክፉም ደግም ቀናት አልፈዋል፤ የማሸነፍን ድል ለመቀዳጀት በመጠንከር በያልፋል ቅኝት ተጉዟል። የትየለሌ ትናንቶቹ ህመም መከፋትና መገፋት አጥልቶባቸው አልፈዋል።

የማትሪክ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# የፍትሕ አካላት የምርመራ ጋዜጠኝነት ሥራን እንዲያግዙ ባለሥልጣኑ ጥሪ አቀረበ

የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለሥልጣን
ETHIOPIAN MEDIA AUTHORITY

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የፍትሕ አካላት የምርመራ ጋዜጠኝነት ሥራን ሊያግዙ እንጂ ሊያደናቅፉ እንደማይገባ የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለሥልጣን አሳሰበ።

ባለስልጣኑ ባወጣው መግለጫ እንዳስታወቀው፤ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ የምርመራ ጋዜጠኝነት ሥራዎች እንዲቆሙ ትዕዛዝ የመስጠት አዝማሚያ እየተስተዋለ መጥቷል።

የመገናኛ ብዙኃን ባለሥልጣን ለመገናኛ ብዙኃን ሥራ አስቻይ ሁኔታ እንዲፈጠር በሕግ የተጣለበትን ኃላፊነት ከመወጣት አንፃር መገናኛ ብዙኃን በሚያከናውኗቸው የምርመራ ጋዜጠኝነት ሥራዎች ላይ በማንኛውም አካል የሚፈጸም ማዋከብ እንዲቆም በመግለጫው አሳስቧል።

የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ 2፤ 3/ለ እና 4 እንዲሁም በመገናኛ ብዙኃን አዋጅ ቁጥር 1238/2013 አንቀጽ 48 መሠረት መገናኛ ብዙኃን የሕዝብን ጥቅም የሚመለከት መረጃ የማግኘት መብት እንዳላቸው መገለጹን ባለሥልጣኑ አስታውሷል።

ለዴሞክራሲያዊ እና ተጠያቂነት ለሰፈነበት ሥርዓት ግንባታ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን የማግኘት እና የመመርመር የአሠራር ነጻነት አልፎ ተርፎም የሕግ ጥበቃ እንደሚደረግላቸው መደንገጉንም ጠቅሷል።

የምርመራ ጋዜጠኝነትን ከማበረታታት አንፃርም ከሕጋዊ ማሕቀፎች ባለፈ እንደ መንግሥት አቅጣጫ

የፍትሕ አካላት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72

ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18

ይዘዙን

ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።

ነገን ዛሬ እንሥራ










የጋራ ምክር ቤቱ የሰላም ስምምነቱ ዘላቂ እንዲሆን እየሰራ ነው

ገጽ 3

# የሰላም ስምምነቱ የተረጋጋ የኢኮኖሚ ሥርዓትን ለመገንባት ይረዳል

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- ተግባራዊ መሆን የጀመረው የሰላም ስምምነት የተረጋጋ የኢኮኖሚ ሥርዓት ለመገንባት የሚረዳ ነው ሲሉ በወሎ ዩኒቨርሲቲ የኢኮኖሚክስ መምህሩ አቶ ተፈራ ጌታቸው ገለጹ።

አቶ ተፈራ ጌታቸው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ በጦርነት ወቅት ከነበረችበት ሁኔታ ይልቅ ወደሰላም ስምምነቱ ከገባች በኋላ በኢኮኖሚው የተሻለ መስራት እንደምትችል ይታመናል።

የሰላም ስምምነቱ ኢንቨስትመንቱን በማነቃቃት፤ ባለሀብቶች የተረጋጋ ስራ እንዲያከናውኑ አስፈላጊ ነው። መንግሥትም በዘላቂነት አገር አቀፍ የኢኮኖሚ ዕቅዶች ላይ ተግባራዊ ለማድረግና ለማሻሻል እንዲያግዘው የሰሜን ኢትዮጵያ ግጭት በሰላማዊ መንገድ መፈታቱ ጠቀሜታው የጎላ ነው።

የሰላም ስምምነቱ የተረጋጋ የኢኮኖሚ ሥርዓት በመፍጠር የቢዝነስ እንቅስቃሴዎች እንዲጠናከሩ ያደርጋል። በስጋት ላይ የነበሩ ስለስራ እንዲያስቡ፤ የተዘጉ ኩባንያዎችም ዳግም ስራ እንዲጀምሩ በማነሳሳት ረገድ የሰላም ስምምነቱ ተግባራዊነት በጎ ተጽዕኖ አለው ሲሉ አስረድተዋል።

በሌላ በኩል ጦርነቱ በነበረበት ወቅት የግብርና ስራቸው ተስተጓጎሎ የነበሩ አርሶአደሮችን ከሰላሙ በኋላ ወደ ግብርና ስራቸው እንዲያተኩሩና ምርታማ እንዲሆኑ ያደርጋሉ ብለዋል።

በዚህ ረገድ አርሶአደሩ የግብርና ስራውን በተጠናከረ ሁኔታ ማከናወን እንዲችል በተለያዩ መንገዶች የፋይናንስ እገዛ ያስፈልገዋል ሲሉ ገልጸዋል።

በርካታ ኃይል የሚሳተፍበት ስራ በማከናወን ምርት የበለጠ እንዲጨምር ማድረግ ከተቻለ ደግሞ ኢኮኖሚውን እየፈተነ የሚገኘውን የአቅርቦትና ፍላጎት አለመጣጣምን በመቀነስ የዋጋ ግሽበቱን ለማረጋጋት ይቻላል ብለዋል።

እንደአገር ከሰሜኑ ጦርነት ወጥተን ወደሰላም በመመለሳችን የመንግሥትም ይሁን የግል ሰራተኛው በአጠቃላይ አምራቹ ኃይል ሙሉ ጊዜውን በስራ እንዲያሳልፍ ይረዳል ሲሉ አስረድተዋል።

እንደ አቶ ተፈራ ገለጻ፤ የፋይናንስ፣ አገልግሎት ሰጪና ሌሎች ከቱሪዝም ጋር የተያያዙ ተቋማትም ወደስራ ስለሚመለሱ ኢኮኖሚው ላይ የማይናቅ በጎ አስተዋጽኦ ማምጣት ይቻላል።

ከዚህ ባለፈ የተፈናቀሉ ዜጎች ወደቀያቸው ተመልሰው መደበኛ ሕይወታቸውን እንዲቀጥሉና ኢኮኖሚው ውስጥ አሻራቸውን ማሳረፍ እንዲችሉ የሰላም ስምምነቱ ተግባራዊነት ጠቀሜታው የጎላ ነው ብለዋል።

አሁን ላይ በጦርነቱ የተነሳ ኢኮኖሚው ምን ያክል ተጎድቷል የሚለውን ማጥናት ይገባል። ከተደራጀ ጥናት በኋላ ቀጥታ ለጦርነት ሲውል የነበረውን ሀብት ወደ ንግዱ፣ ኢንቨስትመንቱና ስራ ፈጠራው በስፋት ማዋል ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

በተጨማሪ ጦርነቱ እንደ መልካም ዕድል በመጠቀም ማህበረሰቡን ሲያማርሩ የነበሩ ነጋዴዎች ላይ ቁጥጥር በማድረግ በጦርነት አካባቢ ላይ የቆየውን የማህበረሰብ ክፍል የተረጋጋ የገበያ ሥርዓት እንዲፈጠርለት ማድረግ ይገባል ብለዋል።

አቶ ተፈራ እንዳስታወቁት፤ በአጠቃላይ የፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት ወደተግባር በመግባቱ የስራ ዕድል ፈጠራ በማጠናከር፣ ምርታማነትን በማሳደግ፣ አቅርቦትን በማሳደግና በተለያዩ አማራጮች ኢኮኖሚው ላይ የሚኖረውን በጎ ዕድል መጠቀም ይገባል።



አቶ ተፈራ ጌታቸው



ፋይል

# ኮርፖሬሽኑ በጦርነቱ በተጎዱ አካባቢዎች የዋጋ ንረትን ለማርገብ እየሰራ ነው

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- በጦርነቱ በተጎዱ አካባቢዎች የተከሰተውን የምርት አቅርቦት እጥረት ለመቅረፍና የዋጋ ንረትን ለማረጋጋት የእህልና የፍጆታ ዕቃዎች ምርት እያቀረበ መሆኑን የኢትዮጵያ ንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን አስታወቀ። ኮርፖሬሽኑ እያቀረባቸው ካሉ ምርቶች መካከል ጤፍ ፣ዘይትና ዱቄት፣ ዋና ዋናዎቹ ናቸው ብሏል።

የኮርፖሬሽኑ ሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ እቴነሽ ደገፉ በጦርነት ጉዳት በደረሰባቸው አካባቢዎች የምርቶቹን እጥረትን ለመቅረፍና የዋጋ ንረትን ለማረጋጋት እየሰራ መሆኑን ገልጸው፤ ለአብነትም በደሴና አካባቢዋ ከሶስት ሺህ 200 በላይ ኩንታል ጤፍ ፣ ዱቄት ፣ ሩዝ ፣ ፓስታ፣ መኮሮኒ፣ ጨውና ፣160 ሺህ ሊትር ዘይት ለግብይት ማቅረቡን ገልጸዋል፡፡

የምርት አቅርቦቱንም ለአላማጣ ከተማ ፣ ራያ አላማጣ፣ ኮረም ወረዳ አስተዳደር፣ ቆቦ ዙሪያ ፣ ራያ ቆቦ፣ ራያ ባላ ወረዳ ፣ ኮረም ከተማ ፣ኮረም ዙሪያ እና ወፍላ ወረዳ አካባቢዎች በመሰራጨት ላይ መሆኑን ኮርፖሬሽኑ ገልጿል።

ምርቶቹ በኮርፖሬሽኑ ደሴ የእህልና ቡና እና ፍጆታ እቃዎች ንግድ ስራ ዘርፎች ግብይት ማእከላት በኩል ከክልሉ መስተዳድር እና ንግድ ቢሮ ሃላፊዎች ጋር በመሆን ለህብረተሰቡ በመኖሪያው አካባቢ ባሉ የገበያ ቦታዎች በአካባቢው ያለውን ችግር ውስጥ ግምት ውስጥ በማስገባት በተመጣጣኝ ዋጋ እየተሸጡ ነው፡፡

ኢፕድ ያነጋገራቸው የአላማጣ ከተማ ንግድ ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ሀብታሙ በርሄ ከኮርፖሬሽኑ የምርት አቅርቦት ድጋፍ እየተደረገላቸው መሆኑን ገልጸው፤ ድጋፉ የገበያ ማረጋጋት ስራቸው ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረገ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ምርቶቹ ለሸማቹ ህብረተሰብም በተመጣጠኘ ዋጋ መቅረባቸውን አመልክተው፣ የምርቶቹ ዋጋ ከተማው ላይ ካለው 50 በመቶ እና ከዚህ በላይ የዋጋ ቅናሽ እንዳላቸው ገልጸዋል፡፡ ኃላፊው አክለውም የዘይት ምርት ካለው ፍላጎት አኳያ አነስተኛ መሆኑንና እምብዛም ነጋዴው ከሚሸጥበት ዋጋ ልዩነት ስለሌለው የዋጋ መስተካከያ እንዲደረግም ጠቁመዋል።

ኮርፖሬሽኑ በተመሳሳይ በሰቲት ሁመራ ዞን አዲ ረመጥ ከተማ ፣ ወልቃይት ወረዳ ፣ ዳንሻ ከተማና በሌሎች በጦርነቱ ጉዳት ለደረሰባቸው አካባቢዎች የፍጆታ ሸቀጦችን ለማቅረብ እየተሰራ መሆኑን ገልጿል።

የኢትዮጵያ የንግድ ስራዎች ኮርፖሬሽን የተመረጡ የግብርና ምርቶችን፣ የፍጆታ ሸቀጦችን፣ የኢንዱስትሪ ምርቶችን እና አትክልትና ፍራፍሬዎችን በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ ገበያን ለማረጋጋት እየሰራ ያለ የፌዴራል መንግሥት የልማት ድርጅት መሆኑ ይታወቃል።

# የኔልሰን ማንዴላ ሙዚየም በቀጣይ ዓመት ለጉብኝት ክፍት ይሆናል

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- የኔልሰን ማንዴላ ሙዚየም በቀጣይ ዓመት ለጉብኝት ክፍት እንደሚሆን የአዲስ አበባ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ገለጸ።

የአዲስ አበባ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ሂሩት ካሳው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፣ ቢሮው ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጋር በተባበር እየሰራ ያለው የሙዚየሙ ላንድስኬፕና ዲዛይን ሥራ በዚህ ወር ተጠናቅቆ ርክክብ ያደርጋል። የእድሳት ሥራዎቹም በተያዘው ዓመት ተጠናቅቆ በሚቀጥለው ዓመት ለጉብኝት ክፍት ይሆናል።

የላንድ ስኬፕ እና ዲዛይን ጥናቱ ሥራ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር ለመስራት የተፈለገበት ዋና ምክንያት ቅርሱን የያዘው ቦታ በጣም ሰፊ በመሆኑና ለጎበኚዎች ምቹ የጉብኝት ቦታ በመሆኑ እንደሆነም ተናግረዋል።

ይህ ታሪካዊ ቦታ የሚገኘው በኮልፌ 18 የፌዴራል ፖሊስ ማሰልጠኛ ግቢ ውስጥ ሲሆን ኔልሰን ማንዴላ ወታደራዊ ሥልጠና ሲወስዱበት የነበረ ቦታ መሆኑም አውስተዋል፡፡

ይዞታውም የፌዴራል ፖሊስ ኮሌጅ ነው ያሉት ዶክተር ሂሩት፤ የሙዚየም ግንባታው በአዲስ መልክ የሚገነባ ሳይሆን የነበረውን ቅርስነቱን አስጠብቆ በውስጡ ያለውን ታሪካዊ የሆነ ኪነ ህንጻ እድሳት በማድረግ ታሪኩን የማስቀጠል ሥራ እንደሆነም አብራርተዋል።

ከዛ በተጨማሪም እነ ሂሩት በቀለ ፣ አለማየሁ እሸቴ እና ሌሎችም ብዙ ታላላቅ አርቲስቶች በዚያ ውስጥ ያለፉና ከዚያ ቤት የወጡ መሆናቸውን የጠቆሙት የቢሮ ኃላፊዋ፤ አሁን እየተሰራ ባለው ሥራ የኔልሰን ማንዴላ ጉዳይ ትልቁን ቦታ የያዘ ሲሆን ታላላቅ አርቲስቶችን የሚያወሱ ቁሶችንና የሙዚቃ መሳሪያዎቻቸው በቅርስነት አንድ ላይ ተደርጎ ለጎብኝት እንዲውሉ የሚያስችል ለማድረግ መታቀዱንም ገልጸዋል።

እንደ ዶክተር ሂሩት ማብራሪያ፣ ሙዚየም የማንዴላን ታሪክ ከመዘከርና ይፋ ከማውጣት አኳያ ጅማሬው ጥሩ ነው። ከደቡብ አፍሪካ የመጡ



ዶክተር ሂሩት ካሳው

ባለሀብቶችና የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ቦታውን ጎብኝተዋል። ከጎበኚዎቹ ጋርም በተደረገው ውይይት ሥራውን ለመደገፍም ፍቃደኝነታቸውን ገልጸዋል።

ሙዚየሙ ከቱሪዝም አንጻር ያለው ጠቀሜታ እጅግ ትልቅ ነው ያት ዶክተር ሂሩት፤ የቱሪስቱን የቆይታ ጊዜ በማራዘም የውጭ ምንዛሪ እንዲጨምር ያደርጋል ብለዋል። ይህ ሙዚየም ለኢትዮጵያውያን ብሎም ለአፍካውያንም ኢትዮጵያ የጋራ ቤታቸው መሆኗን ትልቅ ማሳያ ነውም ብለዋል።

አዲስ አበባ የአፍሪካ መዲናና የአፍሪካ የነጻነት አርማ መሆኗን ለማሳየት የአፍሪካ ሕብረት ብቻ በመዲናዋ መቀመጡ በቂ አይደለም ያሉት ዶክተር ሂሩት፤ ለዚህም ነው እነዚህን ቅርሶች በመጠገን ለጎብኚዎች ክፍት ማድረግ የታሰበው ብለዋል።

አፍሪካውያንም ሆነ የዓለም ጎብኚዎች ወደ ከተማዋ ሲመጡ ከአፍሪካ ሕብረት በተጨማሪ በተጨባጭ ኢትዮጵያ ተከናውነው ያለፉ ክስተቶች ለማሳየት ሙዚየሙ ትልቅ ሚና እንዳለው አመልክተዋል።



## የጋራ ምክር ቤቱ የሰላም ስምምነቱ ዘላቂ እንዲሆን እየሰራ ነው

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ወደ ትግራይ አቅንቶ ከባለድርሻ አካላት ጋር ለመወያየትና  የሰላም ስምምነቱን ለመተግበር በሚደረገው ሂደት ላይ እያጋጠሙ ያሉ ችግሮችን አጥንቶ የመፍትሔ ሃሳብ ለማቅረብ ማቀዱን አስታወቀ፡፡

የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ሰብሳቢ ዶክተር መብራቱ አለሙ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የሰላም ስምምነቱን ተግባራዊ ለማድረግ ብዙ ርቀት እየተሄደ ቢሆንም ሂደቱ አልጋ በአልጋ አይደለም፡፡

በመሆኑም ምክር ቤቱ ወደ ትግራይ አቅንቶ ከባለድርሻ አካላት ጋር ለመወያየትና የሰላም ስምምነቱን ለመተግበር በሚደረገው ሂደት ላይ እያጋጠሙ ያሉ ችግሮችን አጥንቶ የመፍትሔ ሃሳብ ለማቅረብ እንቅስቃሴ መጀመሩን ጠቁመዋል፡፡

የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነቱ እንዲጠናከርና በሕዝቦች ውስጥ የተፈጠሩ ውስጣዊ ቁስለቶችን ለማከም የሚያስችሉ ሥራዎችን መሥራት አስፈላጊ መሆኑን ጠቅሰው፤ በተለይ ሲቪል ማህበራትና ፖለቲካ ፓርቲዎች የሚጠበቅባቸውን ሚና እንዲወጡ መግባባት ላይ ተደርሷል ብለዋል፡፡ ምክር ቤቱም ወደ ትግራይ ክልል አቅንቶ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ለመወያየትና በሂደት እያጋጠሙ ያሉ ችግሮችን አጥንቶ የመፍትሔ ሃሳብ ለማቅረብ አቅዷል ብለዋል፡፡

በመንግሥት በኩልም ስምምነቱን ለመተግበር እየተደረጉ ያሉ ጥረቶችን በተመለከተ ምክር ቤቱ የኢትዮጵያ መንግሥትን ወክለው ስምምነቱን የፈረሙት አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን በተገኙበት ሰፊ ውይይት ማድረጉን ጠቅሰው፤ በውይይቱ መንግሥት እየሄደበት ያለው ርቀት ተስፋ ሰጪ መሆኑን ተገንዝበናል ብለዋል፡፡

በሂደቱ ላይ ሁለቱ ወገኖች እንዳይስማሙና ችግሩ እንዲቀጥል የሚፈልጉ የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች መኖራቸውን እንደታወቀ በመጠቆም፤ ፖለቲካ ፓርቲዎችን ጨምሮ መላው ኢትዮጵያውያን ስምምነቱ ከዳር እንዲደርስ መሥራት እንዳለባቸው መግባባት ላይ መደረሱንም ጠቁመዋል፡፡ የሰላም ስምምነት አተገባበሩ ላይ ግልጽነት በመፍጠር በኩል የሚታዩ ክፍተቶችን መቅረፍና  ስምምነቱን ለመተግበር የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን ይፋ ማድረግ እንደሚገባ ምክር ቤቱ አቋም የወሰደበት ጉዳይ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ለአገር እድገት በሰላም ወጥቶ ለመግባትና  እንደ አገር ልናሳካቸው ለምንፈልጋቸው ጉዳዮች ሁሉ መሳካት ሰላም ምርጫ የሌለው አማራጭ ነው ያሉት ሰብሳቢው፤ ይህን ሰላም የሆነ አካል እንዲያረጋግጥልን የምንተወው ጉዳይ ሳይሆን እያንዳንዳችን በምንጥለው ጠጠር የሚረጋገጥ መሆኑን መገንዘብ አስፈላጊ ነው ብለዋል፡፡ በመልሶ ግንባታ ላይ እየተደረጉ ያሉ ጥረቶችንም ባለሀብቶችና ሌሎችም ዜጎች በሀብታቸው፣ በእውቀታቸውና በጊዜያቸው ሁሉ መደገፍ አለባቸው ብለዋል፡፡

በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል ያለውን ችግር መፍትሔ ለመስጠት የተደረሰው የሰላም ስምምነት በሌሎች የአገሪቱ ክፍሎች የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመቅረፍ ተመሳሳይ ርምጃ በመውሰድ አገራዊ ሰላሙን ሙሉ ለማድረግ እንዲሠራም ዶክተር መብራቱ ጠይቀዋል፡፡

# ስመጥፋት ተቃርበው የነበሩ እንስሳትን ቁጥር ለማሳደግ በተሰራው ስራ ውጤት እየተገኘ ነው

**ሳሙኤል ወንደሰን**



ሚዛን አማን፡- የመጥፋት አደጋ የተጋረጠባቸውና በተፈጥሮ ድርቅንና በሽታን መቋቋም የሚችሉት የሸኮ ጎዳ ዳልጋ ከብቶችን ቁጥር ከ2 ሺህ ወደ 7 ሺህ ከፍ ማድረግ መቻሉን የሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ አስታወቀ።

የሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ምክትል ፕሬዚዳንት ዶክተር አብዮት አስረስ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ቁጥራቸው ተመናምኖ ከ2 ሺህ የማይበልጡ የነበሩት የሸኮ ጎዳ ዳልጋ ከብቶች ቁጥርን ዩኒቨርሲቲው ከ7 ሺህ በላይ ማድረስ ችሏል። ይህም በአምስት ዓመት ውስጥ የመጣ ውጤት ነው።

ከብቶቹ ከፍተኛ የሆነ የወተትና የስጋ ምርት ያላቸው መሆናቸው እና በተፈጥሮ ድርቅንና በሽታን መቋቋም የሚችሉ ዝርያዎች መሆናቸው ከሌሎች ከብቶች የሚለዩበት ባህሪያቸው ነው።

የሸኮ ጎዳ ዳልጋ ከብቶች በተፈጥሯቸው ጉልበተኛና ቁጡ ባህሪ ያላቸው በመሆናቸው አርሶ አደሩና አርብቶ አደሩ እነሱን ከመጠበቅና ከማርባት ይልቅ ለገበያ ማዋልን ይመርጣል። ህብረተሰቡ ከብቶቹን የማይፈልጋቸው በተፈጥሮ ጉልበተኛ መሆናቸውን እንጂ በተፈጥሮ ድርቅንና በሽታን የሚቋቋሙ፣ የወተት ምርታቸው ከፍተኛ እንደሆነና ከፍተኛ የሆነ የስጋ ምርት እንዳላቸው ባለመገንዘብ ነው ያሉት ዶክተር አብዮት፤ ይህን የአመለካከት ችግር ለመቅረፍ የሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ የሸኮ ጎዳ ዳልጋ ከብቶች ጥበቃና ማሻሻያ ፕሮጀክት በመቅረፅ በሠራው ሥራ በአሁኑ ጊዜ ቁጥራቸውን ወደ 7 ሺህ ማድረስ እንደተቻለ አብራርተዋል።

የአካባቢው አርሶ አደርና አርብቶ አደር ዝርያውን አስመልክቶ የነበረውን የተሳሳተ አመለካከት መለወጥ የሸኮ ጎዳ ከብትን ከተጋረጠበት አደጋ ለመታደግ ወሳኝ እንደሆነ በመግለፅም፤ ይህ የሚደረገው ከብቶቹን ከመጥፋት ለመታደግ እና የማህበረሰቡን ተጠቃሚነት ለማሳደግ ነው ብለዋል።

ዶክተር አብዮት፤ ፕሮጀክቱ ውጤታማና የማህበረሰቡን ተጠቃሚነት እያረጋገጠ በመምጣቱ ትልቅ እርካታና ለበለጠ ስራ እንዳነሳሳቸው ተናግረው፤ አርሶ አደሩም የሸኮ ዝርያ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በገበያ ላይ ተፈላጊነቱ እየጨመረ መሆኑን እየተናገረ ነው ብለዋል፡፡

በተለይ የሸኮ ጎዳ ላሞች ከተጋረጠባቸው የመጥፋት ስጋት በአስተማማኝ መታደግ ያስፈልጋል ያሉት  ምክትል ፕሬዚዳንቱ፤ በአርሶ አደሩና አርብቶ አደሩ ውስጥ ስለሸኮ ጎዳ ከብቶች ተመራጭነትና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ የግንዛቤ ማስረጽ  ስራ እየተሰራ እንደሆነና ስራውን ወደ ሌሎች የክልሉ ዞኖች ለማስፋት እንቅስቃሴ መጀመሩን ገልጸዋል።

የሸኮ ጎዳ ከብቶች የተደቀነባቸው የመጥፋት አደጋ በመቀነስ  አስተማማኝ ደረጃ ላይ ለማድረስ ከሌሎች የዘርፉ የአገር ውስጥና የውጭ አገር ተቋማት ጋር ያለው ግንኙነት አጠናክሮ እንደሚቀጥልም ጠቁመዋል።

አሁን ላይ  እንደ አገር  ከ2 ሺህ የማይበልጥ የነበረው የከብቶቹ ቁጥር ከ7 ሺህ በላይ መድረሱን እንደ ትልቅ ስኬት እንደሚቆጠር ገልጸው፤ ይህ ዝርያ ከስጋት ነጻ ነው ለማለት ቁጥሩ ከ10 ሺህ ማነስ እንደማይኖርበት ተናግረዋል።

የሸኮ ጎዳ ዳልጋ ከብቶች በሀገሪቱ በደቡብ ምእራብ ዞኖች የሚገኙ በተፈጥሮ ድርቅንና በሽታን የሚቋቋሙ ሲሆን በወተት ምርታቸውም ይታወቃሉ። ዝርያው በተለይ በሬው  ከፍተኛ ጉልበት ያለው በመሆኑ ለእርሻ ስራ ተመራጭ ነው።



# ሕብረተሰቡ ከሕገ-ወጥ እርድ እንዲታቀብ ኮሚሽኑ አሳሰበ

## - ለገና በዓል እስከ 6 ሺ ከብቶች ለእርድ ሊያቀርብ ነው

**በሪሁ አረጋ**

አዲስ አበባ፡- ሕገወጥ እርድ ከፍተኛ የጤና እክል ሊያስከትል ስለሚችል ማህበረሰቡ ከድርጊቱ ሊቆጠብ እንደሚገባ የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን አሳሰበ፡፡ ለገና በዓል እስከ ስድስት ሺህ ከብቶች፣ ፍየሎችና በጎች ለዕርድ እንደሚያቀርብም ኮሚሽኑ አስታውቋል።

የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን የስጋ ምርመራ አገልግሎት ቡድን መሪ ዶክተር ከበበ ኤርቤቶ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፣ ኮሚሽኑ ከኢትዮጵያ ቄራዎች ድርጅት ጋር በመተባበር ለሚመጣው የገና በዓል የሚውሉ የእርድ እንስሳት አቅርቦት ማስፋትና ቄራው የ 24 ሰዓት አገልግሎት እንዲሰጥ ዝግጅት ላይ ነው።

በተለይ በበዓላት ወቅት ሕገ- ወጥ እርድ ይበዛል ያሉት ዶክተር ከበበ፣ ድርጊቱ በሕብረተሰቡ ላይ ከፍተኛ የሆነ የጤና እክል የሚያስከትል ከመሆኑም ባሻገር በአገር ኢኮኖሚ ላይም አነስተኛ የማይባል አሉታዊ ተፅእኖ አለው ብለዋል።

ሕገ-ወጥ እርድ ምርመራ ያልተደረገላቸውና ጤንነታቸው ያልተረጋገጠ እንስሳትን በማረድ ለሕብረተሰቡ በመሸጥ ተጠቃሚዎችን ለተላላፊ በሽታዎች ያጋልጣል ብለዋል።

ሕገ-ወጥ የእርድ ስራ ከሕግ አስከባሪዎች በመሸሸግ አብዛኛውን ጊዜ ጨለማን ተገን በማድረግ የሚሰራ ነው ያሉት ዶክተር ከበበ፣ በመሆኑም ተረፈ ምርቶችንም በየቦታው በመጣል አካባቢን በማቆሸሽ ብክለትን ያስከትላል ብለዋል።

ሕገ-ወጥ እርድ አገሪቱ ከቆዳና ሌጦ ምርቶች የምታገኘውንም ገቢ በመቀነስ በኢኮኖሚ ዘርፉም እንደ ተግዳሮት የሚወሰድ ነው ሲሉ ዶክተር ከበበ ተናግረዋል።

ዶክተር ከበበ አክለውም፣ ድርጅቱ ለሚመጣው የገና በዓል የ24 ሰዓት የስራ አቅርቦት ለመስጠት እየሰራ መሆኑንም ገልጸዋል፡፡

ለእርድ የሚውሉ እንስሳት ማቆያ ውስጥ እንዲቆዩ በማድረግ ሙሉ ምርመራ ከተደረገላቸው በኋላ ንፅህናውን የጠበቀ ውሃና ምግብ እንዲያገኙ ይደረጋል። ከታረዱ በኋላ ስጋቸውን በሚመረመርበት ጊዜም ጤነኛ ያልሆነ ስጋ ከተገኘ ሙሉ በሙሉ ስጋው ይቃጠላል ብለዋል፡፡

ለመላው የክርስትና እምነት ተከታይ መልካም የገና በዓል እንዲሆንላቸው ዶክተር ከበበ  ተመኝተዋል።

ዜና

# ምሁራን ያላቸውን እውቀትና ጥበብ የማህበረሰቡን ችግር ለመፍታት ሊጠቀሙበት ይገባል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ሐዋሳ፡- ምሁራን ያላቸውን እውቀትና ጥበብ የማህበረሰቡን ችግር ለመፍታት በማዋል ታሪክ የሚዘክር ተግባር ሊያከናውኑ እንደሚገባ የሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ ሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ እና የቱሪዝም ሚኒስትር አምባሳደር ናሲሴ ጫሊ አስገነዘቡ።

የሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ ምሁራን የምክክር መድረክ ላይ ሚኒስትሯ እንደተናገሩት ፤ "ከለውጡ ወዲህ እንደ አገር የተለያዩ ስኬቶች ተቀዳጅተናል፣ ተግዳሮቶችም አጋጥመውናል" ብለዋል።

ያጋጠመውን ችግር ለመሻገር የፖለቲካ አመራሩ ውይይት፣ ውሳኔና ጥረት ብቻ ሳይሆን የሁሉንም አካላት ተሳትፎ ማረጋገጥ እንደሚያስፈልግ የታመነበት መሆኑን ገልጸዋል።

የአገር ጉዳይ ሁሉንም እንደሚመለከት ገልጸው፤ በተለይ ባጋጠሙ ችግሮች ዙሪያ ከምሁራን ጋር መወያየት ቁልፍ መሆኑን አስምረውበታል።

በአገራት ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ምሁራን ሰፊ አስተዋጽኦ ማድረጋቸውን አውስተዋል።

ኢፍትሀዊነትን በመዋጋትና በመጋፈጥ በሀገራት ላይ ፖለቲካዊ ለውጥ እንዲመጣ እና ለማህበራዊ ቀውሶች መፍትሄ በማመንጨት የላቀ ሚና መጫወታቸውን ገልጸዋል።

በመሆኑም ከምሁራን ጋር እየተደረገ ያለው ውይይት ከሁሉም ማህበረሰብበ ጋር ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ጠቅሰው፤ ይህም በቀጣይ ለማካሄድ ለታሰበው አገራዊ ምክክር ትልቅ ግብዓት እንደሚገኝበት ተናግረዋል።

ምሁራን ለችግሮች ተግባራዊ የሚሆን መፍትሄ በማመንጨት በግንባር ቀደምትነት ተጠቃሽ መሆናቸውን አስታውሰው፤ ጥቂት ምሁራን እውቀታቸውንና ጥበባቸውን ለማህበረሰባቸው በማበርከት ታሪክ እንደሚዘከራቸው ጠቁመዋል።

ምሁራን ያላቸውን እውቀትና ጥበብ ማህበረሰቡን ከማንቃትና ከመቀየር ለማህበረሰቡ ችግር መፍትሄ በማፍለቅ ታሪክ የሚዘክር ተግባር ሲያከናውኑ ነው ብለዋል ሚኒስትሯ።

በተለይ ሲንከባለሉ የመጡና ፖለቲካዊ ውሳኔ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች፣ የሞራል ዝቅጠት፣ ሌብነትና ሌሎችም ያሉብንን ሰፊ ችግሮች ለመወጣት የምሁራን ሚና ምን መሆን እንዳለበት ለመምከር ታስቦ መድረኩ መዘጋጀቱን ሚኒስትሯ አስታውቀዋል።

አገሪቱ ካለችበት ችግር ተላቃ ወደ ፊት እንድትጓዝና እንድታድግ ከምሁራን ጋር በሚደረገው ውይይት የሚገኙ የመፍትሄ አመላካች ሃሳቦችን ለፖሊሲ በግብዓትነት እንደሚውል ጠቅሰው፤ ምሁራኑ ጠንካራ ውይይት እንዲያደርጉ አመላክተዋል።

የሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር አያኖ በራሶ በበኩላቸው ከለውጡ ወዲህ የተለያዩ ስኬቶች ቢመዘገቡም በርካታ ተግዳሮቶች በማጋጠማቸው ይህንን ታሳቢ ያደረገ ሀገር አቀፍ ውይይት ከምሁራን ጋር መጀመሩን ጠቁመዋል።

ከዚህ አንፃር ከችግሮች በአፋጣኝ እንድትላቀቅና እንድትሻገር ምሁራን ምርምርና ትንተና በመስጠት ለፖሊሲ አውጪዎች ሃሳብ በማቅረብ ገንቢ ሚና ሊጫወቱ እንደሚገባ አሳስበዋል።

ከምሁራን አገር ከእኛ ምን ትጠብቃለች በሚል የሃሳብ ትግል በማድረግ ሰፋ ያለ አስተዋጽኦ ማድረግ እንደሚጠበቅ ዶክተር አያኖ አመላክተዋል።

ለሁለት ቀናት በተዘጋጀው መድረክ በአገር ግንባታ የምሁራን ሚና በሚል ርእስ የተዘጋጀ ሰነድ ቀርቦ ውይይት እንደሚደረግበት ተገልጿል።

# ውሎና...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

እየተደረገላቸው ነው ብለዋል፡፡

ጊዜያዊ ማገገሚያ ማዕከል እንዲጠለሉ ከተደረጉት ውስጥ ሁለት ሺህ በላይ የሚሆኑት ህፃናት መሆናቸውን የገለጹት ዳይሬክተሩ፤ ሌሎች ቁጥራቸው 52 የሚደርሱ ሕፃናት ደግሞ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን ተቀላቅለው ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ነው ብለዋል፡፡

በተጨማሪም ከ 700 በላይ የሚሆኑ ውሎና አዳራቸውን ጎዳና ያደረጉ ወጣቶችን ከሜድሮክ ኢትዮጵያ ጋር በመነጋገር ወደ ጅማ ሊሙ የእርሻ ልማት በመላክ ወደ ቡና ለቀማ ሥራ እንዲሠማሩ መደረጉንም አብራርተዋል።

እንዲሁም ከ5 ሺህ በላይ የሚሆኑ የጎዳና ተዳዳሪዎች ወደየመጡበት አካባቢ የመመለስ ስራ እንደተሠራ ገልፀው፤ ማህበረሰቡ ለጎዳና ተዳዳሪ ዜጎች ያለው አቀባበል አናሳ በመሆኑ ተመልሰው ጎዳና የወጡ ዜጎች እንዳሉ ጠቁመዋል።

97 በመቶ የሚሆኑ ውሎና አዳራቸውን ጎዳና ያደረጉ ዜጎዎች በቤተሰብ ግጭት፣ በስራ ፍለጋ፣ በወላጅ አልባነትና በሰላም እጦት ምክንያት ከተለያዩ ክልሎች የመጡ መሆናቸውን ያብራሩት አቶ ቢኒያም፤ ቁጥራቸውን ለመግታት ቅንጅታዊ አሠራር እንደሚያስፈልግ አብራርተዋል፡፡

በአሁኑ ወቅትም በአዲስ አበባ አስተዳደርና በክልሎች መካከል የቅንጅታዊ አሠራር ክፍተት በመኖሩ ቁጥሩን ለመቀነስ አለመቻሉን አስረድተዋል፡፡

ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት የፌዴራል መንግሥት ከክልል መንግሥታት ጋር በቅንጅት በመሥራት ከክልሎች ወደ መዲናዋ ለሚፈልሱ ዜጎች የሥራ ዕድል በመፍጠር እና ደጋፍና ክትትል በማድረግ ችግሩን ከምንጩ ማድረቅ እንደሚገባ መልዕክት አስተላልፈዋል።

# የማትሪክ ውጤት...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

በድህነት ፅኑ ክንድ የደቀቀው የግርማ ትከሻ በጸና የህመም ናዳም ተመቶ ያውቃል። በሕይወቱ ሰልፍ እልፍ የመከራ ሰይፍ አልፏል። በምድር ላይ ሲኖር ዓለም የመፈተኛ አይነትና ጊዜዋን በመቀያየር በብዙ ፈትናዋለች። የሕይወት ክፉ ስጦታዎች ያየሉበት ግርማ፤ ብዙ ደግና ክፉ ቀናትን በኑሮው ሲፈራረቁ ከአለት በጠነከረ ልቦና አስተናግዷቸዋል። ትምህርቱን ለመማር ሲል ድንጋይና ሲሚንቶ ተሸካሚ ሆኖ የጉልበት ሥራ ሠርቷል።

ግርማ፣ በኦሮሚያ ልዩ ዞን ፊንፊኔ ዙርያ ሙሎ ወረዳ ሙሎ ሲሎ በተባለች ቀበሌ ነው ይህችን ምድር የተቀላቀለው። ወላጆቹ አቶ ዳባ ደገፋና ወይዘሮ አበራሽ ጉተማ ግብርና መኖሪያቸው ነው። ሆኖም ከእጅ ወደአፍ የዘለለ አይደለም። በዚህ ድህነት በሚያንገዳግደው የቤተሰብ ሕይወት ውስጥ የልጃቸው ግርማ የመማር ጉዳይ የአምስት እህቶችና አንድ ወንድሙን የዕለት ጉርስ ከመቻል እኩል ትኩረት የሚሰጠው አልነበረም። እንዲያውም ከቤተሰቡ መሀል ሁለት እህቶቹ ብቻ እስከ ስድስተኛ ክፍል ድረስ ተምረዋል እንጂ ሌላ በትምህርት ደጃፍ ያለፈም አልነበረም።

ለግርማና ቤቱ መማር ቅንጦት ነበር። እንዲያውም እንደ ልጅ ይሄን አማረኝ ያኛውን እያለ የሚቀብጥበት አልነበረውም። ከብላቴንነቱ ንጋት ጀምሮ ሕይወት ያለ ዕድሜው እየቀጣችና ያለሚዛኑ እየፈተነች በአሳር ገንቢታ እያደነደነችው ነበር። በለጋ ልቡ የሚንተከተከው እልህ በቀላሉ ተሸነፍኩ ባይ እንዳይሆን አድርጎታል። ከጎኑ አለሁ ባይ አልነበረውምና ሕይትወትን ብቻ ለብቻ ግብ ግብ የመግጠም ግዴታው ትከሻውን ተጭኖ አላጎበጠውም። የመጀመሪያው መባቻ ዳዴ በ1993 ዓ.ም ነው የተጀመረው። ከአካባቢው ገበሬዎች ጋር የጎልማሳ ትምህርት ቤት ውስጥ በመማር አሃዱ የተባለው ፍኖት በአስራ ሦስት ዓመቱ ወደ አንደኛ ክፍል በመግባት የዛሬው ስኬት ዘር ሊያጎነቁል በቃ።

ግርማ ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ትምህርቱን ያጠናቀቀው ከክፍሉም ከአጠቃላይ ትምህርት ቤቱ ካሉ ክፍሎችም አንደኛ በመውጣት ነበር። የስምንተኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተናንም 99 ነጥብ ዘጠኝ በማምጣት ማለፍ ችሏል። ዘጠነኛና አስረኛንም ሰኞ ገበያ በተባለ ትምህርት ቤት ውስጥ ተማረ።

ግርማ ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ ራሱን በማገዝ ነው የተማረው። ከአንደኛ እስከ ስድስተኛ ክፍል ግማሽ ቀን እየተማረ ብዙ ጊዜም የቤተሰቡን መሬት እያረሰ ነበር ያሳለፈው። ከስድስትኛ እስከ አስረኛ ክፍል ያለውን ትምህርቱን በከተማ ስላሳለፈ የባለሀብት ልጆችን በማስጠናት ኑሮውን ገፍቷል።

በመምህራን እንዲሁም በሌሎች ቀና አሳቢ ሰዎች ድጋፍ ተምሮ አስረኛ ክፍል ዘጠኝ 'ኤ' በማምጣት ሙሉ አራት ነጥቦችን ማስመዝገብ ችሏል። ጫንጮ ከተማ ላይ የመሰናዶ ትምህርቱን በአባገዳ ትምህርት ቤት ላይ ተምሯል። በዚህ ትምህርት ቤት በመማር ላይ ሳለ ነበር በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ይሉት ነገር ሆኖበት በድህነትና ብቸኝነት ያሳለፈውን የመቸገር ወቅቱን ህመምም ተጨመረበት። የመሰናዶ ትምህርቱ ላይ በቂ ድጋፍ ስላላገኘም ሁለት ጊዜ ተፈትኖ የዩኒቨርሲቲ ማለፍያ ነጥብ ሊያገኝ አልቻለም።

ለትምህርት ፍቅር ልቡን የሰጠው እና ከልጅነቱ ጀምሮ አንደኛ ሲወጣ የኖረው ግርማ በሕይወቱ ወሳኝ ጊዜው ላይ ትምህርትም እንደ ሰው ከዳው። ሰው በሚወደው ቶሎ ተስፋ አይቆርጥምና እርሱም የዛለ ክንዱን አፈርጥሞ ኑሮን መታገል ያዘ። በዚህም ትግል ላይ መርታት ቻለና ተስፋ ሳይቆርጥ ድጋፍ ተደርጎለት እንደገና ለሦስተኛ ጊዜ ተፈትኖ ከ500 በላይ አምጥቶ ማለፍ ቻለ።

ወላይታ ዩኒቨርሲቲ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ገብቶም በመጀመሪያ ዓመት አራት ነ ጥብ አመጣ። ዕድሜውን ሙሉ ስታባርር ያኖረችው ሕይወት አሁንም ልታሳርፈው አልፈቀደችም ነበር። ሌላ የመጎዳት ዘመን ጠበቀው። ሕይወቱን ለመግፋት የሚሰራቸው ስራዎች መደራረብ ለተደጋጋሚ ህመም ዳርገውታል። ሲሠራ ከነበረው ሥራ የተነሳ ከኩላሊት ህመም በተጨማሪ የልብ ህመምተኛ ሆነ።

ሁለተኛ ዓመት ትምህርቱን ከህመሙ ጋር በመታገል ውጤቱ ሦስት ነጥብ ስምንት አመጣ። ታግሎ ትምህርቱን ለመቀጠል ቢፈልግም በኩላሊት ህመም ተሰቃይቶ ትምህርቱን ለማቋረጥ ተገደደ። ወደ ውጪ ሄዶም እንዲታከም ተወስኖ አቅም ስላልነበረው ከተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ገንዘብ ተሰብስቦለት ወደ ውጪ መሄድ ስላልቻለ ጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ሕክምና አግኝቶ የጤናው ሁኔታ ተሻሻለ።

በኋላም ዩኒቨርሲቲው ወደ ትምህርት እንዲመለስ አድርጎ በደንብ ሳይድን እየታመመ ተምሮ በመጨረሻ በመመረቂያ ዓመቱ 37 ኤ+ በማምጣት በጤና ኮሌጅ በፋርማሲ ትምህርት ክፍል ከዩኒቨርሲቲው የወርቅና የዋንጫ ተሸላሚ ሆኖ ከጤና ሚኒስትር ዴኤታ ሽልማቱን ተቀብሏል።

ክፉውን አድልታ በሰጠችው ሕይወቱ ውስጥ በመልካምነት ቀለም ስማቸውን ያተሙ ሰዎችም አልታጡም። ከነዚህ ውስጥ አክስቱ የቅርብ ጓደኞቹና መምህራኑ የሕይወትን መጥፎ ቀናት አለንልህ ብለው ያሻገሩት መርከቦቹ ናቸው። ግርማ በፋርማሲ ስራ ላይ መሰማራት ይፈልጋል፤ ዋንኛ ምክንያቱም ኢትዮጵያ ሀገሩን በዘርፉ በዓለምአቀፍ ደረጃ ተጠሪ ማድረግ ነው። ባህላዊ መድኃኒቶችን በዘመናዊ መንገድ በመቀመም ኢትዮጵያን ለዓለም ማስተዋወቅ ይፈልጋል።

በሁሉም ውስጥ ማለፍ መቻል መልካም ነው ያሳለፍኩት ሁሉ አበርትቶኛል ይላል። ሰው መጠንከር ከቻለ ተስፋን ስንቁ ካደረገና ህልም ካለው የማያልፍ ነገር የለም ዋናው መበርታት ነው ይላል መልእክቱን ሲያስተላልፍ። በርትቶ መስራት የመጀመርያ የትምህርት ሕይወቱን በድል እንዲያጣጥም ያደረገው ግርማ በእሱ ትናንት ላይ ያለውን ክፉ ቀን ዛሬ ለሚኖሩ ሁሉ በርቱ የሚል ምክሩን ለግሷል።

# የፍትሕ አካላት...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ተይዞ እንዲሠራ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተገኝተው ማሳሰባቸውንም ባለሥልጣኑ በመግለጫው ጠቁሟል።

ይህ ሊረጋገጥ የሚችለው ደግሞ መገናኛ ብዙኃን ያለምንም መታወክ እና እንቅፋት ብቁ የምርመራ ጋዜጠኝነት ሥራ መሥራት እንዲችሉ መረጃ የማግኘት፣ የመሰብሰብ፣ የመመርመር እና የማሠራት መብታቸው ከማንም በላይ በፍትሕ አካላት ሲረጋገጥ እና ጥበቃ ሲደረግለት መሆኑን ገልጿል።

ከዚህ በተቃረነ አግባብ የመገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎች የምርመራ ጋዜጠኝነት ሥራ ላይ በማንኛውም መንገድ እክል መፍጠር የዜጎች መብትን መደፍጠጥ፤ የዴሞክራሲ ባህል ግንባታ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ መፍጠር እንዲሁም ተጠያቂነት እንዳይሰፍን ከአጥፊዎች ጋር እንደመተባበር ይቆጠራል ሲል ባለሥልጣኑ አስታውቋል።

በመርሕ ደረጃ የዜጎች መብት የተረጋገጠበት የዴሞክራሲ ባህል የሚጎለብትበት እና ተጠያቂነት የሚሰፍንበት ሥርዓት ለመገንባት የፍትሕ አካላት ከመገናኛ ብዙኃን ጋር እጅና ጓንት ሆነው መሥራት እጅግ ጠቃሚ መሆኑን በመግለጫው ጠቁሟል።

የምርመራ ጋዜጠኝነት ሥራ አጋዥ እና ተዋናይ መሆን የሚጠበቅባቸው የፍትሕ አካላት ለዚህ ሥራ አጋዥ እንጂ እክል እንዳይሆኑ ባለሥልጣኑ ጥሪ አቅርቧል።

# ኢትዮጵያ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

በአገር ውስጥ ለሚደረገው የልማትና የሰላም እንቅስቃሴ ደጋፊ የሆነ የውጭ ድጋፍ ማግኘት ያስፈልጋል። ይህ ትብብር ከጥሩ ጎረቤት አገር መጀመር ይኖርበታል።

ኢትዮጵያ ከጎረቤት አገሮች ጋር በታሪክ፣ በባህልና በተፈጥሮ ሀብት የተሳሰረ ግንኙነት ስላላት አንድነትን የማጠናከር ጽኑ ፍላጎትን ይዛ እየሰራች ነው ያሉት አምባሳደር ይበልጣል፤ የአንዱ ብልጽግና የሌላው በመሆኑና በዛው ልክ የአንዱ ወደ ኋላ መቅረት በሌላው ላይ ተጽዕኖ ስለሚያሳድር ተደጋግፎ መበልጸግና ማደግ ያስፈልጋል ብለዋል።

ኢትዮጵያ የዓባይ ግድብ የአፍሪካውያን ፕሮጀክት ነው ብላ ታምናለች ያሉት አምባሳደሩ፤ ኢትዮጵያ ከሱዳን ጋር የኤሌክትሪክ ትስስር አላት፡፡ ወደ ሱዳን፣ ኬንያና ጅቡቲ ትልካለች። የተጀመረውን የኃይል አቅርቦት ለማሳደግ ከሱዳን ጋር ንግግር እየተደረገበት ነው ብለዋል።

እንደ አምባሳደር ይበልጣል ገለጻ፤ ሱዳንና ኢትዮጵያን በመሰረተ ልማት የማስተሳሰር ስራ እየተሰራ ነው፤ አሁን ያለውን የመንገድ ትስስር ወደ ባቡር ሀዲድ ለማሳደግ ጥረት እየተደረገ ነው። እንዲሁም ከኢትዮጵያ በኩል ወደብ የመጠቀም ፍላጎት አለ፤ በአጠቃላይ ሁለገብ የሆነ ትብብር እንዲፈጠር እየተሰራ ነው ብለዋል።

በሰሜኑ የአገራችን ክፍል ተከስቶ የነበረው ጦርነት በቅርቡ መፍትሔ ያገኘው በአፍሪካ ሕብረት አማካኝነት ነው ያሉት አምባሳደሩ፤ ይህም የአፍሪካውያን ችግሮች በአፍሪካውያን መፈታት አለባቸው ለሚለው ማረጋገጫ ነው ሲሉም ጠቅሰዋል።

በአገራችን የተፈጠረውን ችግር ለመፍታት የደረስንበት ውጤት የአፍሪካ ሕብረት ጥረት ነው። ይህን አቋም ወደ ፊትም ኢትዮጵያ አጠናክራ ትቀጥላለች። የዓባይ ግድብ በሶስትዮሽ ድርድር በአፍሪካ ሕብረት አማካኝነት እንዲፈታ ትሻለች፤ ትሰራለችም ብለዋል።

የዓባይ ግድብ የሶስትዮሽ ውይይት በአፍሪካውያን መፈታት አለበት የሚል እምነትን በማንጸባረቅ አፍሪካ ሕብረት ጉዳዩን በባለቤትነት ይዞ እየሰራበት እንደሚገኝም ገልጸዋል።

እንደ አምባሳር ይበልጣል ማብራሪያ፤ ሱዳን ውስጥ የሚፈጠር ችግር ኢትዮጵያን ይጎዳል። ሱዳን ስትበለጽግ ኢትዮጵያውያን ተጠቃሚ ይሆናሉ። በተመሳሳይ ኢትዮጵያ ውስጥ መልካም እድገት ሲኖር ሱዳናውያን ተጠቃሚ ይሆናሉ። የኢትዮጵያ ፍላጎትና አቋም ሱዳን ሰላሟና አንድነቷ የተጠበቀ አገር እንድትሆን ነው። ከረጅም ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጵያ ለሱዳን ሰላምና አንድነት ድጋፍ ስታደርግ ቆይታለች ብለዋል።

እ.ኤ.አ በ1972 ሱዳን የርስ በርስ ጦርነት ውስጥ ገብታ በነበረበት ወቅት የመጀመሪያው የአዲስ አበባ ስምምነት ተብሎ በሚታወቀው ስምምነት ኢትዮጵያ አደራድራለች። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በኢጋድ አማካኝነት ችግሩ በዘላቂነት እንዲፈታ በግንባር ቀደምትነት ስራ ሰርታለች። የሰላም አስከባሪ ኃይል በዳርፉርና አቢዬ በማሰማራት ሰላም እንዲመጣ ከፍተኛ ሚናን ተጫውታለች ብለዋል።

በሱዳን የአልበሽር መንግሥት መውደቁን ተከትሎ ችግር ሲገጥማቸው ችግሩ በሰላም እንዲፈታ ኢትዮጵያ ያደረገችው አስተዋጽኦ ጉልህ መሆኑን የጠቀሱት አምባሳደር ይበልጣል፤ በሱዳን ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍን ኢትዮጵያ በኢጋድና በአፍሪካ ሕብረት አማካኝነት የማይቋረጥ ጥረት ስታደርግ መቆየቷን ተናግረዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## አገራዊ ሰላሙን ማስቀጠል የእያንዳንዱን ዜጋ ንቁ ተሳትፎ ይጠይቃል!

መንግሥት ያለ አንዳች ቅድመ ሁኔታ ወደ ሰላም ውይይት ለመምጣት የደረሰበትን ውሳኔ ተከትሎ በአገሪቱ ያለው አጠቃላይ ሁኔታ መልኩን ከቀየረ ውሎ አድሯል። በተለይም በአፍሪካ ኅብረት አሸማጋይነት እና በዓለም አቀፉ ህብረተሰብ ድጋፍ የፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት መፈረሙ ሁኔታዎች በፍጥነት መልካቸውን እንዲቀይሩ እያደረገ ነው።

የሰላም ስምምነቱ ሕገመንግሥታዊ ሥርዓትን የኢትዮጵን የግዛት አንድነት እና ብሄራዊ ጥቅምን መሰረት ያደረገና በዚሁ እውነታ ላይ የተመሰረተ መሆኑ፤ በተለይም መንግሥት እንደ መንግሥት የተጣለበትን ሀገራዊ ኃላፊነት በተሻለ ሁኔታ በሰላማዊ መንገድ እንዲወጣ እድል ፈጥሮለታል። አገርን ከተጨማሪ ሰብአዊና ቁሳዊ ውድመት መታደግ አስችሏል። ጦርነቱ በአካባቢው ፈጥሮት የነበረውን ሥነ ልቦናዊ ጫና ለማቃለል ረድቷል።

በተለይም መንግሥት ባለው አቅም ሌሎች የርዳታ ተቋማትን በማስተባበር ለትግራይ ሕዝብ የዕለት ደራሽ የምግብ እህል አቅርቦቶች ያለ ገደብ በስፋት እንዲቀርብ ያሳየው ቁርጠኝነት ፤ ጦርነቱን ተከትሎ ሊፈጠሩ ይችሉ የነበሩ ከዕለት ምግብ እጥረት ጋር የተያያዙ ችግሮችን በአስተማማኝ ሁኔታ መቋቋም አስችሏል።

ከመድሃኒትም ጋር በተያያዘም ሕዝብ በተለይም አስቸኳይ የሆኑ መድሃኒቶችን ፈጥኖ እንዲያገኝ ቀደም ባለው ጊዜ በቂ ዝግጅቶችን አድርጎ እየተገበረ ያለበት መንገድ ፤ አጠቃላይ ከሆነው ሀገራዊ አቅም አንጻር የሚበረታታ፤ ከፍ ያለ እውቅና ሊሰጠው የሚገባ ነው። በቀጣይ ለሚያደርገውም ተጨማሪ ጥረትም የረድኤት ድርጅቶችን ድጋፍ የሚሻ ነው።

ከዛም ባለፈ በሰላም ስምምነቱ ያልተካተቱ ነገር ግን ስምምነቱን በማስፈጸም ሂደት ውስጥ የተሻለ አቅም መፍጠር ያስቻሉ ፤ በእርግጥም በአደባባይ አቅም ሆነው የተገኙ ፤ የመንግሥት የልዑካን ቡድን በመቀሌ ያደረጉት አይነት ጉብኝት፤ የመንግሥትን የሰላም ቁርጠኝነት ከቃላት ባለፈ በተጨባጭ በተግባር ማሳየት ያስቻለ ነው። ለሰላም የቱንም ዋጋ ለመክፈል ያለውን ዝግጁነት ያመላከተ ነው።

ይህ ዓለም አቀፍ እውቅና ጭምር ያገኘው የመንግሥት የሰላም ቁርጠኝነት በሕወሓትም ሆነ በመላው ሕዝባችን ተገቢውን ትርጉምና ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነው። ከመንግሥት የሰላም ቁርጠኝነት በስተጀርባ ስላለው የበለጸገች ሀገር ግንባታ እያንዳንዱ ዜጋ ሊያስብና፤ ሊያሰላስል ተገቢ ነው። ከሰላም ውጪ ይህንን ራዕይ እውን ማድረግ እንደማይቻል ግንዛቤ ሊወሰድበትም ያስፈልጋል።

አሁን ባለው አገራዊ የፖለቲካ አውድ ፣ ብሄራዊ ጉዳያችን ከአሸናፊና ከተሸናፊ ትርክት ያለፈ ፤ ሀገርን አሸናፊ የሚያደርግ አዲስ የፖለቲካ ባህል መፍጠርን መሰረት ያደረገ ነው፤ መንግሥትን እንደ አንድ የለውጥ መንግሥት ቀደም ባለው ጊዜም ሆነ አሁንም ስለ ሰላም እየከፈለ ያለው ዋጋ ይህንኑ እውነታ ታሳቢ ያደረገ ነው።

ይህ ከዚህ ትውልድ ባለፈ ለመጪው ትውልድ የተሻለች /የበለጸገች አገር የመመስረት ራእይ ፤ ከመጣንበት ረጅም የታሪክ ምእራፍ እና በምእራፉ ውስጥ ካሳለፍናቸው አስቸጋሪ ውጣ ውረዶች አንፃር ፤ ከዛም በላይ ከቆምንበት የታሪክ ምእራፍ ተሻግረን ማየት የማይሹ ታሪካዊ ጠላቶቻችን ከፉ ሴራ አኳያ ብዙ ዋጋ ለመክፈል የመገደዳችን እውነታ ብዙም ለጥያቄ የሚቀርብ አይደለም።

ቁጭ ብለን በሰላማዊ መንገድ ተወያይተን መፍታት የምንችላቸው ችግሮቻችን ከእኛ ከራሳችን ቆሞ ቀር የፖለቲካ ባህል (የሴራ ፖለቲካ) አንጻር እኛን ሆነ መጪውን ትውልድ ያልተገባ ዋጋ ሊያስከፍሏቸው አይገባም። ለዚህ ከቀደመው ታሪካችን ብቻ ሳይሆን ከትናንቶችም በአግባቡ ተምረን አገርን ለሚጠቅም ነገር ልንበረታ ያስፈልጋል። የፖለቲካ ግትርነት አገርና ሕዝብ ዋጋ የሚያስከፍልበ እውነታ ዛሬ ላይ ታሪክ ሊሆን ይገባል።

ከዚህ አንፃር ከሁሉም በፊት ለሀገር ለሕዝብ ፤ ከዚያም በላይ ለመጪዎቹ ትውልዶች ያሳስበኛል የሚሉ የፖለቲካ ሃይሎች ሆኑ የትኛውም ዜጋ መንግሥት በአገሪቱ ዘላቂ ሰላም ለማምጣት እየሄደበት ያለውን ቁርጠኝነት መደገፍ እና አብሮት መሰለፍ ይኖርበታል።

ይህ የራስንና የሚወልዷቸውን ልጆች እጣ ፈንታ የመወሰን ያህል ከባድ የሆነ፤ የእያንዳንዱን ዜጋ ንቁ ተሳትፎ የሚጠይቅ አጀንዳ በአግባቡ ትኩረት ሰጥተን ልንከታተለው ይገባል። ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ቀደም ባለው ዘመንም ሆነ አሁን እየተከፈለ ያለው ዋጋ ትርጉም ኖሮት ፍሬ ሊያፈራ የሚችለው ይህንን ማድረግ ስንችል ብቻ ነው !

ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

# ከጦርነት ጥፋት - ከሠላም ጥቅም

**ምህረት ሞገስ**

ሁሉም ነገር ሰላም ሲሆን እጅግ መደሰት አይቀርም። ስለጦርነት ማሰላሰልና ማሰብ ቀርቶ ስለመልካም ስራ ስለዕድገት እያሰቡ ጊዜ ማሳለፍ ትልቅ መታደል ነው። መታደል ብቻ አይደለም ፤ መታደስ ነው። አሁን ኢትዮጵያ ለእንዲህ ዓይነት ዕድል እየቀረበች ይመስላል። ስለጦርነት፣ ስለሞት እና እልቂት የምናወራበት ጊዜ ሊያበቃ ቅንጣት ቀርቶናል። የሰላም ደጃፍ ላይ ደርሰናል፤ እያንኳኳን ነው።

የሁሉም የሰላም በር ሲከፈት፤ ጦርነት ቀርቶ በምትኩ ሰላማዊ ውይይት መስመር ይይዛል። በትዕግስት እና በጥበብ ውይይት ሲካሄድ እና መግባባት ላይ መድረስ ሲጀመር ኢትዮጵያ እየታደሰች ታብባለች። ልጆቿም በእርሷ መደሰት ብቻ ሳይሆን በሀብቷ እየተጠቀምን ኑሯችንን በተድላ እናጣጥማለን። ዓለም ፊቱን ወደ ኢትዮጵያ ያዞራል። ይህ ቀን በፍፁም የሚቀር አይደለም። አሁን ደግሞ የበለጠ እየቀረበ ነው። ምክንያቱም ኢትዮጵያውያን ነቅተናል። ጦርነት እንደማይበጅ ትርፉ ጉዳት መሆኑን ተረድተናል።

ጦርነት ዕድገትን የሚያደናቅፍ ወደፊት ለመጓዝ ጥረት ሲደረግ ወደ ኋላ የሚጎትት መሆኑን አውቀናል። አጉል እልህ እና ጦር እየነቀነቁ ከእኔ ወዲያ ላሳር ማለት ትርፍ እንደሌለው ተገንዝበናል። አሁን የምንፈልገው ከጦርነት ማረፍ እና እፎይ ብሎ ፊትን ወደ ሥራ ማዞር ብቻ ነው። አሁን ምኞታችን ዕድገት ነው።

ፍላጎታችን ሰላም ብቻ ነው። አሁን በጦርነት ስጋት ተወጥሮ ቀኑን ሙሉ ሥራ ሳይሰሩ መዋል ሳይሆን፤ በትክክል ውጤታማ አገልግሎት በመስጠት ወይም ጥራት ያለው ምርት በማቅረብ ለራስና ለአገር የሚተርፍ ሥራን መስራት በሚል ቆርጠን ተነስተናል።

እርግጥ ነው፤ ጦርነት ከሚያስከትለው ሰብአዊና ቁሳዊ ውድመት ባለፈ ማህበራዊ ግንኙነትን ያበላሻል ፤ የአገር ህልውናንም ይፈታተናል። ይህንንም የቅርቡ የትናንት ታሪካችን ተጨባጭ ማሳያ ነው። ታሪካዊ ጠላቶቻችን ባለመደማመጣችን ተፈጠረውን ግጭት እንደ አጋጣሚ ተጠቅመው እስከምን ድረስ እንደሄዱ ለኛ ነጋሪ የሚያስፈልገን ጉዳይ አይደለም።

አሁን በየትኛወም መልኩ የሚፈጠር ግጭት፤ በግጭት ውስጥ የሚጠፋ የሰው ሀብትና የሀገር ንብረት የአገርን እና የሕዝብን ኢኮኖሚ ከማድቀቅ እና ሁሉንም መልካም ጉዞ ወደኋላ ከማስቀረት ውጪ ጥቅም አልባ መሆኑን ተገንዝበናል።

እሳት እንጨት ካላገኘ እንደማይነደው እና እንደማይቀጣጠለው ሁሉ ኢትዮጵያውያን የጦርነት ሃሳብን ከውስጣችን ማውጣታችን ለአገር ሰላም የሚኖረው ጠቀሜታ ከፍተኛ መሆኑን አምነናል። እሳቱም የሚጠፋበትን ዕድል በማመቻቸት ላይ ነን። የሠላምን ትሩፋት ለማጣጣም ጓጉተናል። ሠላም ከሆነ ደግሞ መሰረተ ልማት መገንባት ይቻላል።

ከአዲስ አበባ ጅጅጋ ብቻ ሳይሆን ከአዲስ አበባ አፋር፣ ከአዲስ አበባ ቤኒሻንጉል፣ ከአዲስ አበባ ጋምቤላ፣ ከአዲስ አበባ ደቡብ ኦሞ ከአዲስ አበባ ጎንደርም ሆነ ባህርዳር፣ ከአዲስ አበባ ወለጋም ሆነ ጉጂ በየትኛውም የኢትዮጵያ አካባቢ ፈጣን የባቡር መስመር ለመገንባት እድል ይፈጥርልናል። ከአዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን ከአንዱ ክልል ወደ ሌላው ክልል መስመር ልንዘረጋ እርስበእርስ በሰላም በኢኮኖሚ ለመቆራኘት ያስችለናል።

ይህ የባቡር መስመር ግንባታ ምርት ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ እንዲንቀሳቀስ፤ ሰዎች ከአንድ ክልል ወደ አንድ ክልል ወይም ከአንድ ከተማ ወደ ሌላ ከተማ እንደፈለጉት ተንቀሳቅሰው መኖር እንዲችሉ ያደርጋል። ይህ ሊሆን የሚችለው ሰላም ሲኖር ነው። መሰረተ ልማት የሰላም ትሩፋት ነው።

በኢትዮጵያ መኖር ሲታሰብ አዲስ አበባ ብቸኛ አማራጭ የምትሆንበት ዕድል ይጠባል። ሰው የትም ሰርቶ በፍጥነት የትም አካባቢ ገብቶ ማደር እና መኖር ይችላል። ይህ የሰላም ትሩፋት አዲስ አበባን እና መላው የኢትዮጵያን ክልል ከኢኮኖሚ ችግርም የሚያላቅቅ ይሆናል።

ደግሞ መረሳት የሌለበት ማንኛውም ነገር የሚፈልገውን ካላገኘ መፈለጉን አያቋርጥም። በተቃራኒው በኢትዮጵያ መደብዘዝ የሚደሰቱ፤ በመደብዘዟ ዛሬም እየተጠቀሙ ያሉ፤ ነገ የኢትዮጵያ መጥፋት ደግሞ የበለጠ ተጠቃሚ ያደርገናል ብለው የሚያስቡ ስግብግቦች የዘመናዊ ቅኝ ገዢነት አስተሳሰብ ውስጣቸው የዳበረ የአፍሪካ ጠላቶች በመሙላታቸው እነርሱም ፍላጎታቸውን ለማሟላት ወደ ኋላ አይሉም።

ይህንን የጠላት ፍላጎት ተገንዝበን ጭንቅላታችንን ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለአጠቃላይ ለአፍሪካ ሰላም፤ ለጋራ መግባባት ካላሰላሰልን፤ እግራችን እና እጃችን ብቻ ሳይሆኑ መላው ሰውነታችን በሰላም ሥራ ላይ ካልተወጠረ እንኳን አንድነትን ማጠናከር፤ ዕድገትን ማረጋገጥ እና አፍሪካውያንን ማንቃት ቀርቶ ኢትዮጵያ እንደ አገር እንደምትቀጥል ፤ ስሟም ከዓለም ካርታ ላይ እንደማይጠፋ ማረጋገጥ አዳጋች ነው።

የሰውን ሃሳብ አለመቀበል፤ በተለይ ለራስ አጉል ደረጃ ሰጥቶ መመፃደቅ እና አልሰማም ማለት ሁሉም ነገር የተሳካ እንዳይሆን ያደርጋል። እሳት የላስኩ ፈጣን፣ ጮሌ ወይም በጣም ንቁ ሰው ነኝ ብሎ የሚያምን ሰው በቀላሉ ተታሎ ሊገኝ ይችላል። ሥልጣን ወይም ገንዘብ ፈልጎ ይታለላል። መሳሪያ ይሆናል። ከተራ የቃላት አጠቃቀም ጀምሮ የሚፈፅመው ትልልቅ ስህተት ቅራኔ ፈጥሮ ወደ መበሻሸቅ ያመራል። እንደተለመደው ጦር መማዘዝ ይመጣል። ከጦር መማዘዝ በኋላ የሚመጣው ደግሞ ሞት እና ጉዳት ብቻ ነው። በመጨረሻም የግለሰብ ሞት፤ የቤተሰብ መፍረስ፤ የአገርን የሚያናውጥ አደጋ ይጋረጣል።

ነቅቶ የሌሎችን ሃሳብ አዳምጦ፤ የሌሎችን ቁስል ተረድቶ፤ የሚመጣን ማታለያ አልቀበልም ብሎ፤ ራስን ከስግብግብነት ገድቦ በእውነት ከልብ ስለሰላም እና ስለአገር ጥቅም ብቻ አስቦ መንቀሳቀስ ከተቻለ ትርፉ ትልቅ ነው። አንዱ ሌላውን ካዳመጠ፤ ለሰላም ቅድሚያ ከተሰጠ፤ ሰላም ከተትረፈረፈ እና ሞልቶ ከፈሰሰ የሚገኘው ጥቅም የትየለሌ ነው። እንኳን ኢትዮጵያን የምታክል አገር በተመቸ የአየር ሁኔታ፣ በተትረፈረፈ የተፈጥሮ ሀብት የታደለች አገር ቀርታ፤ እንኳን በተፈጥሮ ሀብት ብዙዎችን የምታጓጓው አፍሪካ ቀርታ በረዷቸው እና ሙቀታቸው ሰው የሚገድል የተፈጥሮ ሀብት ያልታደሉ አገሮች እንኳን የዓለም ሃያል ለመሆን በቅተዋል።

እነርሱን ከኢትዮጵያ ከአፍሪካ የሚለያቸው ምክንያት አንድ እና አንድ ብቻ ነው። ካለፈው መጥፎ ታሪካቸው ተምረው እርስ በእርስ ጦርነት ውስጥ ለመግባት ጊዜያቸውን እና ጉልበታቸውን አያባክኑም። ትኩረታቸው የራሳቸውን አስተማማኝ ሰላም ማረጋገጥ እና በተለያየ መንገድ ሀብት መሰብሰብ ብቻ ነው።

ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳንሆን አፍሪካውያን ደግሞ ጦርነት ውስጥ በመግባት የያዝነውንና ያለንን መበተን መለያችን ሆኗል። አሁን ግን መፍትሔው ሰላም ነው። ጦርነት ብዙ ጉዳት ማስከተሉ እንደማይቀር ሁሉ ከሰላም የሚገኘው ጥቅም ብዙ ነውና ለሰላም ቅድሚያ መስጠት ይሻላል። ይህ ሲታሰብ በእርግጥ ያለፈው ሁሉ አልፏል። ከአሁን በኋላ ግን መላው ኢትዮጵያውያን ለሰላም ቅድሚያ መስጠት ይኖርብናል። ሰላም!

# ነፃ ሃሳብ

# የሰላም ዋጋው ስንት ነው ?

እስማኤል አረቦ

የሰሜን ዕዝ ጥቃትን ተከትሎ ጥቅምት 24 ቀን 2103 የኢትዮጵያ መንግስትና ህውሓት የለየለት ጦርነት ውስጥ ገቡ። በሁለት አመታት ውስጥም ለሶስት ጊዜያት ያህል ተከታታይ ጦርነቶች ተካሂደው የበርካታ ሰው ህይወት ተቀጥፏል፤መጠነ ሰፊ ንብረትም ወድሟል። በአጠቃላይ በሰውና በንብረት ላይ በደረሰው ውድመት ኢትዮጵያ ክፉኛ ተጎድታለች። በትግራይ፤አማራና አፋር የደረሰውም ከሁሉም የከፋ ነው።

ኢትዮጵያውያን የጀግንነት ታሪክ ያላቸውና ጠላቶቻቸውንም አሳፍረው የመመለስ አኩሪ ታሪክ ቢኖራቸውም የእርስ በእርስ ግጭትና ጦርነትን በሰላማዊ መልኩ የመፍታት ጉልህ ታሪክ አልነበራቸውም። ይልቁንም ሁሉንም ነገር በሃይል የመፍታት ዝንባሌ በአመዛኙ ይታይባቸዋል።

እንደ ህዝብ ሁሉንም ነገር በነፍጥ ብቻ እንፈታለን የሚል ዘመናትን የተሻገረ አስተሳሰብ ስናራምድ ቆይተናል። በጦርነት አንዱ ድል አድራጊ ሌላው ድል ተደራጊ፤አንዱ አሸናፊ ሌላው ተሸናፊ እስካልሆነ ድረስ ጥማችንን አንቆርጥም። የፈለገውን ያህል የሰው ህይወት ቢጠፋ፤ንብረት ቢወድም፤ዜጎች ቢራቡ ፤ቢሰደዱና ቢፈናቀሉ ጦርነት በአንዱ ድል አድራጊነት አስካልተደመደመ ድረስ ማባርያ የለውም።

ሁሉም በየፊናው ግፋ በለው በማለት ማባርያ ወደ ሌለው ዕልቅት መጓዝና በመጨረሻም መቆርቆዝ ለዘመናት ስንመላለስበት የቆየነው ጎዳና ነው። የኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ትልቁ ጉድለት የመነጋገር ባህል አለመለመዱ ነው። ተፎካካሪን እንደ ጠላት ማየትና ማሳደድ ለዓመታት የተፀናወተ ልማድ ነው። በመሠረታዊ ጉዳዮች ላይ ተነጋግረው የጋራ ችግሮችን ለመፍታት ከሚጥሩ ይልቅ የሃይል አማራጭን ቀዳሚ ምርጫቸው አድርገው ኖረዋል ።

በጠረጴዛ ዙሪያ በሚደረጉ ውይይቶች ሊፈቱ የሚችሉ ችግሮች ኃይልና ጉልበት እንደ መፍትሄ በመወሰዱ ምክንያት ከአንድ ትውልድ ወደ ሌላው እየተሻገሩ የጥላቻ፣ የቂም በቀልና የሴረኝነት መነሻ ይሆናሉ። መደማመጥ በሌለበት መተማመን ስለማይኖር የአገር ችግሮች የመፍትሔ ያለህ እያሉ ዓመታት ይነጉዳሉ። መነጋገርና መወያየት በሌለበት ድግሞ መጨረሻው ጦርነት ነው። ጦርነት ድኅ አውዳሚና ለየትኛውም ወገን ውድቀትን የሚያስከትል ነው።

የኢትዮጵያ መንግስትና ህወሓት ግን ይህንን የታሪክ ሰባራ ጠግነውታል። ለሁለት አመታት የዘለቀውን ደም አፋሳሽ ጦርነት በውይይት ለመፍታት በመወሰናቸው አዲስ ምዕራፍ ሆኖ በታሪክ ተመዝግቧል። በአፍሪካ ህብረት ጥላ ስር በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶርያ በተካሄደው የሰላም ስምምነት ሁለቱም ወገኖች ታሪክ ጽፈዋል። አስራ ሁለት አንቀጽ ያለው የሰላም ስምነምነት በማውጣት ሰላምን አውጀዋል።

በፕሪቶርያ የተካሄደው ስምምነት ለዘመናት መፍትሄን በጠብመንጃ ለማምጣት ሲኬድበት የነበረውን ኋላ ቀር አስተሳሰብ የሰበረና ስልጡን የሆነ አካሄድን ለሀገራችን ያስተዋወቀ ነው። ስምምነቱ የኢትዮጵያን መሰረት ከማጽናቱም ባሻገር በጦርነት ሰቆቃ ውስጥ የነበሩትን የትግራይ፤የአማራና የአፋር ህዝቦችን እፎይታ አጎናጽፏል።

ከፕሪቶሪያው ስምምነት ቀጥሎ የተካሄደው የናይሮቢ ስምምነት መተማመንን የፈጠረና ኢትዮጵያ የጀመረችውን የሰላም መንገድ የሚያጸና ነው። በፕሪቶርያው ስምምነትና እሱን ተከትሎ በናይሮቢ በተካሄደው የማስፈጸሚያ ውል ባለፉት ሁለት ዓመታት ከደረሰው ዕልቂት፣ ውድመትና ምስቅልቅል ውስጥ መውጣት የሚያስችል ዕድል ተገኝቷል።

ከስምምነቱ በፊት የነበረውን የትግራይ ህዝብ

**ሰላም ከግለሰብ አልፎ እንደ ሀገር ጥቅሙ ዘርፈ ብዙ ነው። ለጦርነት ይውል የነበረውን ኢኮኖሚ ይታደጋል፤ኢንቨስትመንትና ቱሪዝምን ያበረታታል፤ዜጎች በሀገራቸው ላይ ተረጋግተው እንዲሰሩና ትርፋማ እንዲሆኑ ያስችሳል፤ሀገር ከድህነት ወጥታ በብልጽግና ጎዳና እንድትጓዝ መንገድ ይጠርጋል**

ሁኔታ ብንመለከተው ሰላም ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ በቀላሉ እንድንረዳ ያስችለናል። በሰሜን ኢትዮጵያ የተከሰተውን ጦርነት ተከትሎ የትግራይ ገጠሮችና ከተሞች በጦርነት መታመስ ጀመሩ። በርካታ ወጣቶችም መሳርያ ታጠቁ። በተለይም በከተሞች አካባቢ ሰላምና መረጋጋት ጠፋ። ነዋሪዎችም የሰላም እጦት አንጃበባቸው ፤በሰላም ወጥቶ መግባት ብርቅ ሆነ። በተለይ ባለፈው ዓመት ሰኔ ወር ላይ የትግራይ ኃይሎች በድጋሚ መቀለ ሲገቡ "እነዚህን ሁሉ ታጣቂዎች እንዴት መቆጣጠር ይቻል ይሆን?" የሚል ስጋት በርካቶች ያነሱት ጉዳይ ነበር። በወቅቱ ክልሉ ውስጥ ባሉ የተለያዩ ከተሞች ውስጥ ከነትጥቃቸው የሚታዩ ወጣቶች የስጋቱ ምንጭ እንደነበሩ ነዋሪዎች ይናገራሉ።

በበርካታ የትግራይ ከተሞች በተለይ ደግሞ በመቀለ የሚታዩ የሌብነትና የዘረፋ ወንጀሎች በርካታዎችን ያስጨነቀ ጉዳይ ነበር። በከተማዋ ውስጥ ዘረፋና ለዘረፋ ሲባል አስከ ግድያ የሚደርሱ ወንጀሎች እየተፈፀሙ እንደነበረ ነዋሪዎች ለቢቢሲ ተናግረዋል።ወጥቶ መግባት ብርቅ ነበር። የመንገድ ላይ ንጥቂያ፣ በሥራ ቦታ ስርቆት እንዲሁም ዘረፋ ያጋጥማል።

በየሰፈሩ የተቧደኑ ወጣቶች 'አለው' ብለው የጠረጠሩት ግን ምንም የሌለውን ሰው ሳይቀር አደጋ ያደርሱበታል" ።የተለያዩ ነገሮችን ከሰዎች እጅ ላይ ለመዝረፍ ሲባል ሕይወት የሚያጠፋበት ሁኔታ በከተማዋ ውስጥ የተለመደ ነበር። ሠራተኞች ያለ ደሞዝ ለሁለት አመታት ያህል ለመኖር ተገደዋል። ፣ ነጋዴዎች የሚሸጡት ሸቀጥ አጥተው ሱቆቻቸው ባዶ የሆነበትና የቀን ሠራተኞች ሥራ ፈትተው እርዳታ የሚጠብቁበት ሁኔታ ተፈጥሯል።

ከታሪካዊው የፕሪቶርያው ስምምነት በኋላ ግን ነገሮች ተለውጠዋል። የትግራይ፤የአማራና የአፋር ገጠሮችና ከተሞች ከጦር መሣሪያ ጩኸት ለመገላገል ችለዋል። በአጠቃላይ ኢትዮጵያ እፎይ አለች። ከሰሞኑ ደግሞ በአፈ ጉባኤ ታደሰ ጫፎ የተመራ ልኡካን ቡድን መቀሌን መርገጡ ደግሞ በሰላም ስምምነቱ ላይ የነበረውን ጥርጣሬ ወደ መተማመን እንዲሸጋገር አድርግጓል። የተቋረጡ መሰረተ ልማቶች ሰብአዊ ድጋፎችም በተጠናከረ ሁኔታ እንዲቀርቡ ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል።

በተለይም በጦርነቱ ምክንያት የተቋረጡ መሰረተ ልማቶችንና ሰብአዊ ድጋፎችን በሚፈለገው መልኩ ማድረስ ተችሏል። አስከአለፈው ዕሮብም 105ሺ.910 ቶን ምግብ ነክ እና 8ሺ 624 ሜትሪክ ቶን ምግብ ነክ ያልሆኑ ድጋፎች ወደ ትግራይ የተላከ ሲሆን ከ780 ሺ 755 ሊትር ነዳጅ ተጓጉዟል። በጥሬ ብር ደረጃም ከ800ሚሊዮን ብር በላይ ድጋፍ ተደርጓል።

በተጨማሪም የሰላም ስምነቱን ተከትሎ 80 የትግራይ ከተሞች የኤሌትሪክ ኃይል ተጠቃሚ ሆነዋል። መቀሌን ጨምሮ 27 ከተሞች የቴሌኮም አገልግሎት ተጠቃሚ ሆነዋል። ባንክን በተመለከተም ከ22 በላይ የንግድ ባንክ ቅርንጫፎችን ስራ ለማስጀመር በመጨረሻው ምዕራፍ ላይ ይገኛሉ። የኢትዮጵያ አየር መንገድም ከ18 ወራት በኋላ ወደ መቀሌ በረራ ጀምሯል።

ታህሳስ 19/ 2015 ዓ.ም ለመቀለ ነዋሪዎች የተለየች ነበረች።ለአስራ ስምንት ወራት ተቆራርጠው የነበሩ ቤተሰቦች ተገናኝተዋል።ደም አፋሳሹን ጦርነት ተከትሎ ትራንስፖርትም ሆነ መሰረታዊ አገልግሎቶች በተቆረጡባት ትግራይ ክልል በረራ እንደገና ተጀምሯል። የበረራ አገልግሎት መጀመሩን ተከትሎ ከአዲስ አበባ ቦሌ አየር ማረፊያ እኩለ ቀን ላይ የተነሳው አውሮፕላን መቀለ ካረፈ በኋላም በተለያዩ ስሜቶች የተዋጡ መንገደኞች ታይተዋል።መንገደኞችም በመቀለ አሉላ አባነጋ አየር ማረፊያ ሲደርሱም መሬቱን ሲሳለሙ፣ በርካቶች ሲላቀሱ፣ ሲተቃቀፉም ታይተዋል።ለአንድ ዓመት ተኩል ያላይዋቸውን ቤተሰቦች፣ ወዳጆች ዘመዶችም ጋር አንገት ለአንገት ተቃቅፈው ሲላቀሱ ተስተውለዋል።

በአጠቃላይ በኢትዮጵያ የሰላም አየር መንፈስ በመጀመሩ ዜጎች ወደ ተረጋጋ ህይወታቸው መመለስ ጀምረዋል። መቀሌ ያሉት ወደ አዲስ አበባ ፤አዲስ አበባ ያሉት ወደ መቀሌ መንቀሳቀስና ለሁለት አመታት የናፈቋቸውን ዘመዶቻቸውን በማግኘት ላይ ናቸው። በትግራይ አሻቅቦ የነበረውም የሸቀጦች ዋጋ ከሰላም ስምምነቱ በኋላ መውረድ ጀምሯል። 18ሺ ደርሶ የነበረው የመቶ ኪሎ የጤፍ ዋጋ አሁን ወደ 5ሺ ብር ወርዷል። የተለያዩ የፍጆታ ዕቃዎችም በተመጣጣኝ ዋጋ እየቀረቡ ነው።

ይህ ነው የሰላም ትሩፋት። ዜጎች የሰላም አየር እንዲተነፍሱ፤ከቦታ ወደ ቦታ በቀላሉ ተንቀሳቅሰው እንዲሰሩ፤እንዲማሩ፤ እንዲኩሉ፤እንዲድሩ ያስችላቸዋል። ሰላም ከግለሰብ አልፎ እንደ ሀገር ጥቅሙ ዘርፈ ብዙ ነው። ለጦርነት ይውል የነበረውን ኢኮኖሚ ይታደጋል፤ኢንቨስትመንትና ቱሪዚምን ያበረታታል፤ዜጎች በሀገራቸው ላይ ተረጋግተው እንዲሰሩና ትርፋማ እንዲሆኑ ያስችላል፤ሀገር ከድህነት ወጥታ በብልጽግና ጎዳና እንድትጓዝ መንገድ ይጠርጋል።

ኢትዮጵያውያን ባለፉት ሁለት አመታት የጦርነትን አስከፊነት በውሉ ተረድተውታል። ጦርነት ልዩነትን የሚያሰፋ፤ጠላትነትን የሚፈጥርና ጥላቻን የሚያነግስ ነው። ለዘመናት በአብሮነት የኖሩ ዜጎች በጦርነት ምክንያት የተሳሰሩበት ገመድ ሊላላ ብሎም ሊበጠስ ይችላል። የሰላም ስምምነቱ በጦርነቱ ምክንት ተፈጥሮ የቆየውን የሕዝቦች መራራቅ መልሶ ለመቀጠልና ኢትዮጵያዊነት ቦታውን እንዲይዝ ያደርጋል። የህዝቦች የእርስ በእርስ ትስስር መልሶ እንዲጠናከር በር ይከፍታል። በቀልና ቁርሾን ይሽራል። ጠላትን ያሳፍፍራል፤ወዳጅን ያኮራል።

ጦርነት የሀገርን ገጽታ ያበላሻል። የውጭ ጣልቃ ገብነትንም ያበረታታል። ስለዚህም ሰላም ውይይቱ መተግበር መጀመሩ ላለፉት ሁለት አመታት ጎድፎ ነበረውን የኢትዮጵያ ገጽታ መ ልሶ እንዲታደስ ያደርጋል። በዚህም ሸሽ ተው የቆዩ የውጭ ኢንቨስተሮች መልሰው ወደ ኢትዮጵያ እንዲያማትሩና ኢኮኖሚውም እንዲነቃቃ ያደርጋል። በሰላም ዕጦት ምክንያት ፊታቸውን አዙረው የነበሩ ቱሪስቶችም መልሰው ኢትዮጵያን እንዲጎበኙ ዕድል ይሰጣል።

ሆኖም ሰላምን መጠበቅና መንከባከብ ካልተቻለ መልሶ በጦርነት አዙሪት ውስጥ የመግባት አጋጣሚ ሊኖር ይችላል። በተለይም እንደ ኢትዮጵያ ዘመናትን በጦርነት ውስጥ ለቆየ ሀገር ዘላቂ የሆነ የጦርነት ማስወገጃ ስልት መንደፍ ከመንግስት የሚበቅ ቢሆንም ዋነኛው የሰላሙ ባለቤት የሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ ግን የተገኘውን ሰላም ጠብቆ የማቆየት ግዴታ አለበት።

የኢትዮጵያ ህዝብ በየዘመናቱ በሚነሱ ጦርነቶችና ግጭቶች ሰለባ ሲሆን የቆየ በመሆኑ ከእንግዲህ ወዲህ ችግሮችን በውይይት ከመፍታት ባሻገር ጦርነት ጊዜው ያለፈበት አማራጭ መሆኑን መንገድ ማመላከት አለበት፤አሻፈረኝ የሚሉትንም አንቅሮ ሊተፋቸው ይገባል። በህዝብ ተቀባይነት የሌለው አካል ያለመውን እኩይ ሃሳብ ማስፈጸም አይችልምና የጦርነትና የግጭት እሳቤ ያላቸው አካላት ከእንግዲህ ወዲህ በኢትዮጵያ ምድር ስፍራ ሊኖራቸው አይገባም።

ኢትዮጵያ በርካታ የቤት ስራዎች ያሉባት ሀገር ነች። እነዚህ የቤት ስራዎች ሊሰሩ የሚችሉት ደግሞ ሰላም ሲኖር ነው። ስለዚህም የአገር ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ወገኖች በሙሉ ለመነጋገርና ለመደማመጥ ጊዜ መስጠት አለባቸው። በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ፅኑ የሆነ የምግብ ችግር አለ። የኑሮ ውድነቱ እየባሰበት ነው። የሥራ አጥነቱ መጠን በፍጥነት እያሻቀበ ነው። የአገሪቱ የዕዳ ጫና ከባድ ነው። ጥራት ያለው የትምህርትና የጤና አገልግሎት ተደራሽነት በጣም ዝቅተኛ ነው። በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት በተፈጥሮ ሀብቶች ላይ ከፍተኛ ጉዳት እየደረሰ ነው። በገጠርም ሆነ በከተማ የሚኖሩ በርካታ ሚሊዮኖች ከድህነት ወለል በታች ይኖራሉ። እነዚህን ችግሮች መፍታት የሚቻለው ሰላም ሲኖር ነው።

በ21ኛው ክፍለ ዘመን ህዝብ የሚጠይቀው አንድ ነገር ብቻ ነው። ሕዝብ የሚፈልገው ሰላሙን በዘለቄታዊነት የሚያረጋግጥለት፣ ከድህነት አረንቋ ውስጥ የሚያወጣውና ነገን ብሩህ የሚያደርግለትን አካሄድ ነው። እናም በዚህ መንገድ ኢትዮጵያ መጓዝ ጀምራለች።

ኢትዮጵያ በጦርነት ውስጥ ሆና በግብርናና በአካባቢ ጥበቃ ትንግርታዊ ለውጦችን ማስመዝገብ ችላለች። ስንዴ ከራሷ አከልፎ ወደ ውጭ ለመላክ በመጨረሻው ምዕራፍ ውስጥ ትገኛለች። በአካባቢ ጥበቃ ረገድም በአራት አመታት ውስጥ ከ25 ቢሊዮን በላይ ችግኞችን በመትከል አለምን አስደምማለች። እነዚህ ስኬቶች ሌሎች ተጨማሪ ስኬቶችን እንዲወልዱ አሁን የተፈጠረውን አንጻረዊ ሰላም በዘላቂነት ማስጠበቅ ይገባል።

በፕሪቶርያ የተካሄደው የሰላም ስምምነት ታሪካዊና ለኢትዮጵያም ዘላቂ ሰላም የማስፈን አቅም ያለው ነው። በጦርነት ውስጥ ለነበረው ህዝብም ትልቅ መድህን ይዞ ከመምጣቱም ባሻገር በታሪክም ተጽፎ ለትውልድ የሚተላለፍ ነው። ይህንኑ መነሻ በማድረግ ይመስላል የፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት በቀጣዩ የአፍሪካ ሕብረት ጉባዔ በተሞክሮነት እንደሚቀርብ በአፍሪካ ሕብረት የፖለቲካ ፣ የሰላም እና ደኅንነት ጉዳዮች ኮሚሽነር አምባሳደር ባንኮሌ አዲዎዬ የተናገሩት ።

የሰላም ዋጋ ምን ያህል እንደሆነ ከትናንትም ሆነ ከዛሬ ታሪካችን ከኛ በላይ ሊያውቅና ሊረዳ ይችላል ብሎ ማሰብ ከየዋህነት በላይ ሞኝነት ነው ፤ከዚሕ ተጨባጭ እውነታ በመነሳት በሀገራችን የሰፈነውን አንጻራዊ ሰላም አስጠብቆ ወደ ተሻለ ደረጃ ለማድረስ ሁላችንም መረባረብ ይጠበቅብናል ።ለዚህ ደግሞ የእለት ተእለት አእም ሯዊ እና መንፈሣዊ ዝግጁነት ያስፈልገናል።

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## ተገልጋዮችን ከእንግልትና ካልተገባ ወጪ የታደገው፣ ስራን ያሳለጠው የኤሌክትሮኒክ አገልግሎት

**ወርቅነሽ ደምሰው**

የመንግሥት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ለዜጎች የሚሰጧቸው አገልግሎቶች ብዙ ምልልሶችና እንግልቶች የበዛባቸው፤ ለአላስፈላጊ ወጪና ለምሬት የሚዳርጉ የቅሬታ ምንጭ ሆነው ቆይተዋል። ይህን አሰራር ለመለወጥ የሚያስችሉ ስልቶች በመቀየስ የሕዝቡን ቅሬታ ለመፍታት ሲሰራ ቢቆየም፣ ከችግሩ ግዝፈትና ስፋት አኳያ በሚፈለገው መልኩ የዜጎችን ምልልሶችና እንግልቶች እንዲሁም የሀብትና ጊዜ ብክነትን ማስቀረት ሳይቻል ቀርቷል ።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በአገልግሎት አሰጣጡ ረገድ የተለያዩ የአሠራር ማሻሻያዎች እየተደረጉና መሻሻሎች እየታዩም ናቸው። ምስጋና ለቴክኖሎጂ ይሁንና አሁን ቴክኖሎጂን በመጠቀም የአገልግሎት አሰጣጡን ለማዘመን እየተሰሩ ያሉ ሥራዎች መሻሻል እየታየባቸውና ተስፋ ፈንጣቂ እየሆኑ መምጣታቸውንም ነው መረጃዎች የሚያመለክቱት።

ባለንበት የዲጅታል ዘመን የዜጎችን ኑሮ ቀላል በማድረግ ፈጣን ፣ጊዜንና ወጪን የሚቆጥብ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም እጅግ ወሳኝ ነው። ሀገራችን እየተገበረችው በሚገኘው የአሥር ዓመቱ መሪ የልማት እቅድ ላይ እንደተመላከተው፤ በኢትዮጵያ ዲጅታል ኢኮኖሚን ለመገንባት ያለመውን ግብ ለማሳካት የተቋማትን አገልግሎት አሰጣጥ በማዘመን ወደ ዲጅታል መቀየር ልማት እንዲፋጠን ማድረግ ነው። ይህንን እቅድ ከግብ ለማድረስ አገልግሎቶችን ማዘመን ያስፈልጋል፤ ይህ ስራ ወጪ ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ዜጎች ለእንግልት ሳይዳረጉ ባለቡት ሆነው አገልግሎቶችን በቀላል ዘዴ እንዲያገኙ ለማድረግ የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎች በማልማት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግን ይጠይቃል።

ቴክኖሎጂዎችን የማልማት ኃላፊነት የተሰጠው የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን በማልማት ጥቅም ላይ እንዲውሉ እያደረገ ይገኛል። ከእነዚህ ውስጥም አንዱ የአገልግሎት አሰጣጥን የሚያዘምኑ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የወረቀት ሥራን በማስቀረት አገልግሎቶችን ማሻሻል የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎች በማበልጸግ ሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ ነው።

በዚህም የመንግሥት ተቋማትን አገልግሎት አሰጣጥ ለማዘመን የሚያስችል የአንድ መስኮት አገልግሎት ወይም ኢ-ሰርቪስ( eservices) አገልግሎት ሥራ እንዲውል አድርጓል። ይህንን ቴክኖሎጂ እየተጠቀሙ ያሉ የመንግሥት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በኢ-ሰርቪስ ዘዴ/ ፕላትፎርም/ በኤሌክትሮኒክስ ተጠቅመው አገልግሎት አሰጣጣቸውን እያዘመኑ ናቸው። አገልግሎት አሰጣጣቸውን በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ/ ኢ-ሰርቪስን/ ያደረጉ ተቋማት ደግሞ የክፍያ ሥርዓታቸውን በማስተሳሰር አገልግሎት አሰጣጣቸውን ወደ ከፍተኛ ደረጃ ለማድረስ እየሰሩ ይገኛሉ።

በዛሬው የሳይንስና ቴክኖሎጂ አምዳችን የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ያበለጸገው የኤሌክትሮኒክስ /ኢ-ሰርቪስ/ አገልግሎት በምን ሁኔታ ላይ እንዳለ ፤ አገልግሎት አሰጣጣቸውን በኢ-ሰርቪስ ያደረጉ ተቋማት እንዴት እየተጠቀሙበት ስለመሆናቸው ዳሰናል።

### የኤሌክትሮኒክስ አገልግሎት/ ኢ-ሰርቪስ/

የኤሌክትሮኒክስ አገልግሎት/ ኢ-ሰርቪስ/ ማለት ዜጎች ከመንግሥት ተቋማት የሚፈልጉትን አገልግሎት ባሉበት ቦታው ሆነው በበይነመረብ (በኢንተርኔት) አማካይነት ማግኘት የሚችሉበት ነው። የኢ-ሰርቪስ አገልግሎት አሰጣጥ ከዚህ በፊት ዜጎችን ለእንግልትና ለምልልስ የሚዳርጉ አሠራሮችን በመቀየር አገልግሎቶችን ወደ አንድ በማምጣት በኤሌክትሮኒክ ዘዴዎች ተጠቅመው አገልግሎት እንዱሰጡ ያስችላል። ይህ ደግሞ ከዚህ በፊት ዜጎች አገልግሎቱን ለማግኘት የሚያጠፉትን ጊዜና የሚያወጡትን ያልተገባ ወጪ በማስቀረት ባሉበት ቦታ ሆነው የሚፈልጉትን የትኛውንም አይነት አገልግሎት እንዲያገኙ ያስችላል።

የኢ-ሰርቪስ አገልግሎት የሦስትዮሽ ጥምረትን ይፈልጋል፤ አገልግሎት ፈላጊ ዜጎች /የህብረተሰብ ክፍሎችን/፤ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት እና ቴክኖሎጂውን የሚያቀርቡ አካላትን አንድ ላይ አጣምሮ የሚይዝና ቅንጅታዊ ሥራ የሚጠይቅ ነው።

ኢ-ሰርቪስ አገልግሎት ፈላጊ አካላት ባሉበት ሆነው በሞባይል ፣ በላፕቶብ ወይም በማንኛውም ኢንተርኔት መጠቀም የሚያስችል ቁስ ተጠቅመው የሚፈልጉትን አገልግሎት መጠየቅ የሚችሉበት ነው። አገልግሎት ፈላጊዎች www.eservices.gov.et የሚለውን ጽረገጽ በመጠቀም ለአገልግሎት አሰጣጡ አስፈላጊ የሆነ መረጃዎች በፕላት ፎርሙ ላይ ይጫኑና ጥያቄያቸውም በአገልግሎት ሰጪ ተቋማት በኩል ይታያል፤ አስተያየት የሚያስፈልገው ከሆነ ባሉበት ሆነው በዚያው በፕላት ፎርም አማካይነት ምላሽ እንዲያገኙ ይደረጋል። በመቀጠልም ክፍያ የሚያስፈልግ ከሆነ ክፍያ የሚከፍሉበትን ዘዴም እዚያው ላይ ያገኛሉ። ይህንን ሁሉ ከፈጸሙ በኋላ በመጨረሻም የሚደርሳቸውን አጭር የጽሑፍ መልዕክት በመያዝ አንድ ጊዜ ብቻ አገልግሎቱን ወደ ሚፈልጉበት ተቋም ይሄዳሉ።

ቴክኖሎጂውን በማልማት ለተቋማት የሚያቀርበው የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ተቋማት ለተጠቃሚዎች የተሻለ አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉባቸው ሁኔታዎች ቀልጣፋ እንዲሆኑ ለማድረግ እየሰራ ይገኛል። በዚህ በኢ-ሰርቪስ /ፕላትፎርም/ አገልግሎት እስካሁን 25 ተቋማት የተካተቱ ሲሆን፣ 326 አገልግሎቶች በቀጥታ ስርጭት/ በኦንላይን አገልግሎት እየተሰጡ ናቸው። በእነዚህ አገልግሎቶች ውስጥ የክፍያ ሥርዓት አብሮ እንዲሰጥ ለማድረግ በተሰራው ሥራ ከክፍያ ሥርዓት ጋር የተሳሰሩ አገልግሎቶች ይኖራሉ። ቀሪዎቹን ደግሞ ከክፍያ ሥርዓት ጋር የማስተሳሰር ሥራ እየተሰራ መሆኑን ነው የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ መረጃ የሚያመላክተው።

### የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ተቋማት

የኤሌክትሮኒክ አገልግሎትን ከተቀላቀሉት ተቋማት መካከል የመንግሥት ግዥና ንብረት ባለስልጣን አንዱ ነው። የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ቴክኖሎጂውን ካለማው በኋላ ባለስልጣኑ የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች ወደ ኢ-ሰርቪስ ሲስተሙ በማስገባት ቀዳሚ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆኑን የህዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ዳይሬክተሩ አቶ ሰጠኝ ገላን ገልጸዋል።

አቶ ሰጠኝ እንዳብራሩት፤ አሁን ላይ ወደ 72 የሚደርሱ ተቋማት በቋሚነት አገልግሎቱን እየተጠቀሙ ናቸው፤ 123 ጨረታዎች በጽረ ገጻቸው www.Egp.ppa.gov.et በቀጥታ ስርጭት /በኦንላይን/ ላይ ይገኛሉ። የባለስልጣኑ ድረገጽ ሲከፈት የሚያሳየው የጨረታዎችን ብዛት፣ እየተገመገሙ ያሉ ጨረታዎችን ፣ ምንያህል አቅራቢዎች እንደተመዘገቡ እና የመሳሰሉትን መረጃዎች ነው። በዚህ አሠራር በመጠቀም እስካሁን ድረስ ወደ 292 ጨረታዎች ወጥተዋል። 5ሺ540 የሚሆኑ አቅራቢዎች ተመዝግበዋል፤ ይህ የሚያሳየው አሠራሩ ግልጽነት የተሞላበትና ትስስር ያለው እንደሆነ ነው።

የኤሌክትሮኒክስ አሠራር ብዙ ለውጦችን ያመጣና ጊዜን የሚቆጥብ እንዲሁም ጥራት የሚጨምር ነው ያሉት አቶ ሰጠኝ፣ ጨረታው ለሁሉም ክፍት በመሆኑ ሁሉም መሳተፍ ይችላል ሲሉ ይጠቁማሉ። ይህ መሆኑም የተጫራቾች ቁጥር እንዲጨምር ያደርጋል፤ የተጫራቾች ቁጥር ሲጨምር በአነስተኛ ዋጋ የማቅረብ ሁኔታ ስለሚጨምር ለመንግሥት የሚያስገኘው ጠቀሜታም ይጨምራል። ሙስናንም ሙሉ ለሙሉ ማጥፋት ይቻላል ባይባልም፣ በጣም መቀነስ ይቻላል ሲሉ አብራርተዋል።

የኤሌክትሮኒክ ዘዴን በመጠቀም አገልግሎት መስጠት በርካታ ጠቀሜታዎች እንዳሉት የሚናገሩት አቶ ሰጠኝ፤ የክፍያ ሥርዓቱም ቢሆን ከባንክ ሲስተም ጋር የተያያዘ ክፍያ እንደሆነ ይገልጻሉ። በዚህ ሂደት የጨረታው አሸናፊዎች ወደ ተቋማት (ጨረታውን ወደ አወጣው አካል ዘንድ) መሄድ የሚጠበቅባቸው እቃ ለማቅረብ ብቻ መሆኑን ጠቅሰዋል።

ተቋማት አገልግሎታቸውን ወደ ኤሌክትሮኒክ ዜዴ ከመቀየራቸው በፊት የለመዱትን አሰራር በመከተል በፍጥነት ቴክኖሎጂውን ለመቀበል ተቸግረው እንደነበር የሚያስታውሱት አቶ ሰጠኝ ፤ ይህም ተቋማት ለቴክኖሎጂው ሰጥተው የነበረው ትኩረት አነሳ መሆኑን እንደሚያሳይ ይናገራሉ። አሁን ላይ ግን ተቋማትን ወደ ሲስተሙ እንዲገቡ ግፊት በማድረግ ብዙ ተቋማት ወደ ሲሰተም እንዲገቡ እየተደረገ መሆኑን ያመለክታሉ።

በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ አገልግሎት እየሰጡ ያሉ የተቋሙ ተገልጋዩች አገልግሎቱን አስመልክቶ እየሰጡ ያሉት አስተያየት አበረታች ነው ያሉት አቶ ሰጠኝ፤ ተገልጋዩች ጊዜያቸውን እና ወጪያቸውን እንደቆጠበላቸው መግለጻቸውን ይናገራሉ ። ለአብነት የባለስልጣኑ ተገልጋዮች የጨረታ ሰነድ ለመግዛት እንዲሁም ጋዜጣ ለማገላበጥ የሚያወጡትን ወጪ ጊዜና ጉልበት የቀነሰላቸው መሆኑን በመጥቀስ፣ አገልግሎቱን ሊቀጠል የሚገባው ሲሉ መግለጻቸውን ነው አቶ ሰጥኝ ያብራሩት።

እስካሁን ወደሲስተሙ ያልገቡ ተገልጋይ መኖራቸውን የጠቆሙት አቶ ሰጠኝ፣ እነዚህ አካላት በሀገራችን ብዙ አቅራቢዎች ያሉ ሲሆን የመንግሥት ግዥ ባለስልጣን ኢ ጂፒ ፖርታል/ e-GP Portal /ገብተው ሲመዘገቡ ብቻ ነው ጨረታ ላይ መሳተፍ የሚችሉት ይላሉ፣ ይህን አውቀው ራሳቸውን ከመዘናጋት ማውጣት እንዳለባቸው አስታውቀዋል።

የኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝና የኦዲት ቦርድ ዋና ዳይሬክተር ሂክመት አብደላ በበኩላቸው፤ ተቋሙ ከተመሰረተ ሁለት ዓመት እንዳልሞላው ጠቅሰው፣ በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ሰርቨር በመጠቀም ወደ ኢ-ሰርቪስ አገልግሎት በመግባት አገልግሎቱን በመጠቀም ተቋሙ ቀዳሚ ከሆኑት ተርታ መሰለፉን ይናገራሉ።

> **በ2015 በጀት ዓመት መጨረሻ ወደ 700 /ሰባት መቶ/ የሚሆኑ የኤሌክትሮኒክስ አገልግሎቶችን በማልማት ወደ ሥራ ለማስገባት እየተሰራ ነው። 2ሺ 500 አገልግሎቶች ወደ ዲጅታል የሚቀየሩ ሲሆን፣ ይህም 85 በመቶ የሚሆነውን ተገልጋይ የኤሌክትሮኒክስ አገልግሎት ተጠቃሚ ማድረግ ያስችላል**

እሳቸው እንደሚሉት፤ ኢ-ሰርቪስ አገልግሎት የተቋማቸውን አገልግሎት አሰጣጥ እያዘመነና ቀልጣፋ እያደረገ ነው። ተቋሙ የኢ-ሰርቪስ አገልግሎት ከጀመረ በኋላ ሲቸገር የነበረው የክፍያ ሥርዓት አብሮ ባለመካተቱ እንደነበር አስታውሰው፣ የክፍያ ሥርዓቱን ከቴሌብር ጋር በማስተሳሰር አገልግሎት መስጠት እንዲጀመር መደረጉ ለችግሩ መፍትሔ መገኘቱን አመላክተዋል።

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ሁሉንም የመንግሥት አገልግሎቶች ለዜጎች ተደራሽ ለማድረግ እና ዜጎች ባሉበት በአጭር ጊዜ አገልግሎት ማግኘት የሚያስችል የአንድ መስኮት አገልግሎት ዘዴ በማልማት ሁሉም ማህበረሰብ ተጠቃሚ እንዲሆን እየሰራ እንዳለ ይታወቃል። የኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ የመንግሥት ተቋማትን የአሠራር ሥርዓት በማዘመን ቀልጣፋ አሰራር እንዲኖር የሚያግዝና ዜጎች የመንግሥት አገልግሎቶችን በቀላሉ የሚያገኙበትን ዘዴ በመቀየስ ምቹ፣ ቀልጣፋና ተጠያቂነት ለማምጣት የሚያስችል ዘዴ ነው።

በሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያው ኢትዮጵያ የእድገት ግቦቿን ለማሳካት ሁሉን አቀፍ ዲጅታል ኢኮኖሚ መፍጠር እንደሚያስፈልጋት የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ዴኤታ ሁሪያ አሊ ይናገራሉ።

በመንግሥት ተቋማት ኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን /አይ.ሲ.ቲን/ በመጠቀም በርካታ ሥራዎች ተሰርተዋል። ከእነዚህም ሥራዎች ውስጥ የብሔራዊ የኤሌክትሮኒክስ አገልግሎት አስተዳደር ሥርዓት ዘዴ /ፕላትፎርም/ ወይም የአንድ መስኮት የኢ-ሰርቪስ አገልግሎትን ማጎልበት ይገኝበታል። ይህ የአሠራር ሥርዓት የመንግሥት ተቋማት የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂን በመጠቀም በኤሌክትሮኒክስ የታገዘ የቀጥታ /የኦንላይን/ አገልግሎት እንዲሰጡ የሚያስችል የመረጃ ሥርዓት በመዘርጋት ለዜጎች የሚሰጡ አገልግሎቶች የተሳለጡ እንደሆኑ የሚያስችል መሆኑን ሚኒስትር ዴኤታዋ አብራርተዋል።

እሳቸው እንደሚሉት፤ በሀገራችን የተጀመረው የኤሌክትሮኒክስ አገልግሎት አሰጣጥ የመንግሥት አገልግሎቶችን በቀጥታ /ኦንላይን/ መስጠት ከማስቻሉ ባሻገር መረጃዎችን ዲጅታል ማድረግና ሰነድን ማስቀመጥ ያስችላል። ተገልጋዮች አገልግሎት ለማግኘት ወደ መንግሥት ተቋማት የሚደርጉትን አላስፈላጊ ምልልስ መቀነስ እና በጊዜ ሂደት ምልልስ እንዳይኖር ለማድረግም ያስችላል።

ይህ አሠራር በኤሌክትሮኒክስ አገልግሎቶች የተለያዩ ተቋማት የመረጃዎችን አሰጣጥ አገልግሎት ተናባቢ እንዲሆን የሚያደርግ መሆኑን ሚኒስትር ዴኤታዋ ጠቅሰው፣ የመንግሥት ተቋማትም ለሚያቀርቡት አገልግሎት የተሰጡ አስተያየቶችንና ግብረ መልሶችን በቀላሉ ለማወቅ እንደሚያስችላቸው ይናገራሉ። ለአብነትም መረጃዎች ግልጽና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ በቀላሉ ለህብረተሰቡ ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ እንደሚያስችልም ያመለክታሉ።


ሚኒስትር ዴኤታዋ እንዳሉት፤ ይህ የኢ-ሰርቪስ አሰራር /ፕላትፎርም/ www.eservices.gov.et በሚል ድረገጽ አድራሻ ውስጥ በመግባት የተለያዩ ተቋማት አገልግሎቶችን ወደዚህ ፕላት ፎርም በማስገባት ለደንበኞቻቸው አገልግሎት እንዲሰጡ ያስችላቸዋል ። በሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያው የአሥር ዓመት የልማት እቅድ መሠረት በ2015 በጀት ዓመት መጨረሻ ወደ ሰባት መቶ የሚሆኑ የኤሌክትሮኒክስ አገልግሎቶችን በማልማት ወደ ሥራ ለማስገባት እየተሰራ ነው። 2ሺ 500 አገልግሎቶች ወደ ዲጅታል የሚቀየሩ ሲሆን፤ በዚህም 85 በመቶ የሚሆነውን ህብረተሰብ ክፍል የኤሌክትሮኒክስ አገልግሎት ተጠቃሚ ማድረግ ይቻላል።

በዚህ መሠረት በርካታ ተቋማት አገልግሎታቸውን ለህብረተሰቡ እያሳወቁ እንደሚገኙ የተናገሩት ዴኤታዋ፤ የክፍያ ሥርዓት ትስስሩም ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር የሚፈጠር መሆኑን አመላክተዋል። ዜጎች በአገልግሎት ብቻ ሳይሆን የክፍያ ሥርዓቱን በቀጥታ /በኦንላይ/ በቴሌ ብር አማካይነት እንዲያገኙ መደረጉ አገልግሎት አሰጣጡን ቀልጣፋ እንዲሆን እና በአገልግሎት አሰጣጥ ረገድ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመቀነስ እንደሚያስችል ገልጸዋል።


ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ ትንታኔ

# የሰላም ስምምነቱ መሬት እንዲረግጥ የመንግስት ቁርጠኝነት



ዶክተር አረጋዊ በርሄ



ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ



ኡስታዝ ካሚል ሸምሱ

**አስመረት ብስራት**

የቀድሞው የናይጄሪያ ፕሬዚዳንት ኦሉሴጎን ኦባሳንጆ የኢትዮጵያ መንግስትና ህወሓት በፕሪቶሪያው የሠላም ስምምነት ላይ መድረሳቸውን ይፋ ካደረጉ ታህሳስ 23 ቀን 2015 ዓ.ም. ሁለት ወር ሞላው። በሁለት ወራት ውስጥ የሰላም ስምምነቱን ለማፅናት የተለያዩ ተግባሮች ሲከናወኑ ከመቆየታቸውም በላይ ሰሞኑን በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ በአቶ ታገሰ ጫፎ የሚመራ ከፍተኛ የመንግሥት የልዑካን ቡድን ወደ መቀሌ መሄዱ መንግስት ለሰላም ያለውን ቁርጠኝነት ያሳየ መሆኑን የሚያመላክት ነው።

መንግስት የሰላም ስምምነቱ መሬት እንዲረግጥ ባሳየው ቁርጠኝነት ዙሪያ ያነጋገርናቸው ፖለቲከኛና የህዳሴ ግድብ ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ፅህፈት ቤት ዋና ዳይሬክተር ዶክተር አረጋዊ በርሄ፤ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል ኡስታዝ ካሚል ሸምሱና የኢትዮጵያ ሶሻል ዴሞክራቲክ ፓርቲ (የኢሶዴፓ) ፕሬዚዳንት ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ መንግስት ለሰላሙ መፅናት እያደረገ ያለው እንቅስቃሴ የሚያስመሰግነው መሆኑን ይናገራሉ።

ዶክተር አረጋዊ በርሄ መንግስት ከመጀመሪያው ጀምሮ በክልሉ የተነሱ ችግሮችን በሰላም ለመፍታት በርካታ ጥረቶች ሲያደርግ መቆየቱን ይናገራሉ። ጦርነቱ ከመጀመሩም በፊት ሆነ ከተጀመረ በኋላ ሽማግሌ በመላክ፤ የተለያዩ አለም አቀፋዊ የማህበረሰብ ተቋማትን በማሰማራት፤ ከሁሉም የማህበረሰብ ክፍል አባላት፣ታዋቂ ሰዎች ጭምር ሽምግልና በመላክ ተደጋጋሚ ሙከራ ሲያደርግ መቆየቱን ፤ ከዛኛው ወገን ተቀባይነት ያላገኘበት ሁኔታ እንደነበረ አስታውሰዋል። በጦርነቱ ህይወት ከጠፋና ንብረት ከወደመ በኋላም ቢሆን ለሰላም እጅ መዘርጋት መቻሉ መልካም መሆኑን በመጥቀስ ለህዝብ የሚጠቅም ነገር መደረጉ የመንግስትን የሰላም ፍላጎት የሚያሳይ ነው ይላሉ።

ከሁለት አመታት በኋላ የአፍሪካ ህብረት ጥሪን በመቀበል ወደ ፕሪቶሪያ በመሄድ ስምምነት ላይ መደረሱ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያዊያን የሚበጅ፤ የሀገርን ሉአላዊነት ፈር የሚያስይዝና ለሁሉም እፎይታ የሚሆን ሁኔታ የፈጠረ መሆኑን ይናገራሉ። ይህ የሰላም ስምምነት በተለይም ለትግራይ ህዝብ ታላቅ እፎይታን የፈጠረ ሲሆን፤ ሁሉም አካላት ያሳዩት የሰላም ስምምነቱ መሬት ላይ ወርዶ የሚተገበር ሊሆን እንደሚችል የሚያሳይ ተስፋ መኖሩን ነው።

ዶክተር አረጋዊ፤ የፌዴራል መንግስት ከፍተኛ የልዑካን ቡድን ከሁለት ዓመት በኋላ ወደ መቀሌ ማቅናት የሁለት ወገኖች ስምምነት በተግባር እየዋለ ነው አይደልም? የሚለውን በቅርበት ለመከታተልና ለማወቅ ያስችላል ይላሉ። በሰላም ስምምነት ላይ ምንም አይነት ጥርጣሬ ሳይኖር በፌደራል መንግስቱ ባለስልጣናት ማህበራዊም ኢኮኖሚያዊም ጉዳዮች ላይ የሚታየው ሂደት ምን እንደሚመስል፤ የጎደሉና ያልተስተካከሉ ጉዳዮች ካሉ እሱን ለማቅናት መሄዳቸው ተገቢና የሚደገፍ ተግባር መሆኑን ነው የሚናገሩት።

የሰላም ስምምነቱ ለትግራይ ህዝብ ብቻ ሳይሆን ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ትልቅ እፎይታን የሚሰጥ ነው። የትግራይ ህዝብ ለሁለት አመታት፤ ወጣቱ ከትምህርት ገበታው ርቆ ቆይቷል፤ ነዋሪው ያለስራ በስጋት እየኖረ፤ ሁሉም አይነት አገልግሎቶች በተቋረጡበት በጨለማ እየዳከረ የእውር ድንብር መኖራቸው አብቅቶ ወደ ሰላም መግባቱ ታላቅ እመረታ ነው። ይህ ከብዙ መስዋዕትነት በኋላ የተገኘን ወርቃማ ሰላም ደግሞ መንከባከብ ግድ ነው ብለዋል።

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል ኡስታዝ ካሚል ሸምሱ በበኩላቸው፤ የፌዴራል መንግስት ከፍተኛ የልዑካን ቡድን ከሁለት ዓመት በኋላ ወደ መቀሌ ማቅናት የሰላም ስምምነቱ ተግባራዊነት አበረታች ደረጃ ላይ መሆኑንና መንግስት ለሰላም ያለውን ቁርጠኛ አቋም ያመላክታል ይላሉ።

ከሁለት ዓመታት በኋላ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ በአቶ ታገሰ ጫፎ የሚመራ ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች የልዑካን ቡድን ወደ መቀሌ መሄዱ ልዩ ደስታን የፈጠረ ሲሆን የልዑካን ቡድኑ ወደ መቀሌ ማቅናት ሰላምን ከማብሰር በዘለለ በወረቀት ላይ የሰፈረው የሰላም ስምምነት ተግባራዊነቱ ወደ መሬት መውረዱን፣ ለትግራይ ሕዝብ የሚደረገው ሰብዓዊ እርዳታ ከሪፖርት ባሻገር በተጨባጭ ምን እንደሚመስል እና የመሰረተ ልማቶችን ግንባታ መገምገም እንደሚጨምር ተናግረዋል።

ያለፉት ሁለት አመታት የፈተናና የሩጫ ጊዜ የነበር መሆኑን ያስታወሱት ኡስታዝ ካሚል፤ በተሰራው ዲፕሎማሲያዊ ስራ ችግሮች እየተፈቱ ወደ መደበኛ አሰራር መመለስ እየተቻለ ነው ብለዋል።

ጦርነቱ በተለይ ለኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ትልቅ ፈተና ሆኖ ቆይቷል። ያም ሆኖ በህዝቡ፣ በሰላም አስከባሪ ሀይሎችና ዲፕሎማቶች እልህ አስጨራሽና የተባበረ አንድነትና ጥረት ፈተናዎች መፈታታቸውን ገልጸዋል።

በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል የነበረው አለመግባባት በስምምነት እልባት ማግኘቱ ከዚህ በኋላ በኢትዮጵያ ውስጥ የትኛውም ኃይል በንግግር ካልሆነ በቀር በጦርነት ማሸነፍ እንደማይችል እንዲሁም ሌሎችም ወደ ሰላም እንዲመጡ መንገድ ያሳየ ክስተት መሆኑን ይናገራሉ። በደቡብ አፍሪካ የተደረገው የሰላም ስምምነት በር ከፋችና መላውን ሰላም ወዳድ የኢትዮጵያን ሕዝብ ያስደሰተ እንደመሆኑ የአሁኑ የልዑካን ቡድኑ ወደ መቀሌ መጓዝም ለመላ ኢትዮጵያውያንና ለውጭ ኃይሎች ትልቅ ትርጉም ያነገበ ነው ብለዋል።

በተለያዩ አገራት የሰላም ስምምነት ተደርጎ ግማሹ ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ተግባራዊ የተደረገ፣ ግማሹ ደግሞ ያልተሳካበት ሁኔታ በመኖሩ በእያንዳንዱ እንቅስቃሴ ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ አለበት ፤ ከዚህ አንጻር ግለሰቦችና ሚዲያዎች የነበረውን ቁስል ከሚያስታውሱና ጠላትነትን ከሚያባብሱ ነገሮች መቆጠብ አለባቸው የሚል አስተያየት ሰጥተዋል ።

የኢትዮጵያ ሶሻል ዴሞክራቲክ ፓርቲ (የኢሶዴፓ) ፕሬዚዳንት ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ በበከሉላቸው፤ መንግስት ሰላሙን ለማፅናት የሚያደርጓቸው እንቅስቃሴዎች የሚደገፍና ይበል የሚያሰኝ ነው ይላሉ። መላው የሀገሪቱ ህዝቦች የሚፈለጉት ሰላም ነው። ሰላምን ደግሞ ካልተንከባከቡትና የሚያስቀጥልን ነገር ካልሰሩ ሰላም ሊመጣ አይችልም። ይህንን ደግሞ መንግስት በመረዳት ሰላምን ላለማደናቀፍና ቀጣይነቱን ለማረጋገጥ የመንግስት ባለስልጣናትም ሆነ ሰላማዊው ህዝብን ያካተተ የሰላም እንቅስቃሴ መደረጉ ታላቅ ደስታን እንደሚፈጥር ይናገራሉ።

የመንግስት የልዑካን ቡድኑ የመቀሌ ጉዞ ለሰላም ቅድሚያ የሰጠ በፍፁም የሰላማዊነት መንፈስ በህዝብና ህዝብ መካከል ፈርሶ የቆየውን የግንኙንት ድልድይ የጠገነ በመሆኑ ታላቅ ስኬት ነው ።

ማንኛውም አካል ከሰላም ለመሸሽ የሚደረድረው ምክንያት እንዳይኖር ቀጥተኛና ቀና መንገዶችን በመምረጥ ክፍተትን መድፈን ያሻል የሚሉት ፕሮፌሰሩ የህዝቡ ኑሮ መኖር ወደ ሚገባው ሰላማዊ ሁኔታ ለመቀየር መንግስት ያሳየው ቁርጠኝነትም እጅግ ታላቅ ተግባር ነው ብለዋል።

በህገ መንግስቱ መሰረት ሁሉም የፌደራል መንግስቱ አካላት የሆኑ ክልሎች በሙሉ በፌደራል መንግስቱ መተዳደር አለባቸው የሚለውን ሀሳብም ለማስቀጠል ይህን የሚያረጋግጥ ስራ እየተሰራ ነው። ህዝቡ ጦርነት ሰልችቶት ሰላም በሚሻበት ጊዜ ላይ መደረሱም ለህዝቡ የሚገባውን ሰላም ለመስጠት ምቹ መደላድልን ይፈጥራል።

> **የመንግስት የልዑካን ቡድኑ የመቀሌ ጉዞ ለሰላም ቅድሚያ የሰጠ በፍፁም የሰላማዊነት መንፈስ በህዝብና ህዝብ መካከል ፈርሶ የቆየውን የግንኙንት ድልድይ የጠገነ በመሆኑ ታላቅ ስኬት ነው**

ለቀጣይ መፍትሄ ነው ያሉትን ሀሳብ ፕሮፌሰር በየነ ሲያስቀምጡ ትናንት በስህተት ብዙና ያለተገባ ዋጋ ከፍለናል፤ ከጦርነት ይልቅ የሰላሙን መፍትሄ እስከ ጥግ ድረስ የሚታይበት ሁኔታ መፈጠር ይኖርበታል።

ጥያቄ ያላቸውም አካላት በሰላማዊ መልኩ ጥያቄያቸውን ቢያቀርቡ፤ መሪው አካልም እነዚህ ባለጥያቄ አካላት የሚያቀርቡት ጥያቄ ከህገ መንግስት አንፃር ምን ፍሬ አለው ብሎ በመቃኘት የሚያቀራርቡ ሀሳቦች ላይ ትኩረት መስጠት ተገቢ ነው ይላሉ።

አሁንም ወደ ሰላም ስምምነቱ ሲገባ የተለያዩ ጉዳዮች በሂደት ሊፈቱ በይደር ተከድኖ የተቀመጠና ቅድሚያ ለሰው ህልውና መስጠት ያለውን አማራጭ አይተው ቀሪ የቤት ሥራዎችን በሂደት ከመደርደሪያ ላይ በማንሳት ለመፍትሄ ትኩረት የሚሰጥበት ሁኔታ ተዘጋጅቶ ወደ ሰላም ተገብቷል። አሁንም ግን ዳግም ስህተት ውስጥ ላለመግባት በሰከነ አእምሮ ማሰብ ለሁሉም ሰላማዊ ግንኙነት ውጤታማ ያደርጋል ብለዋል።

ዶክተር አረጋዊ በርሄ በበኩላቸው ፤በቀጣይ የትግራይ ህዝብ ከጎረቤቶቹ አፋርና አማራ ህዝብ ጋር ቀደም ሲል የነበረውን የሰላም፤ የልማት ሁኔታ ከፍ አድርጎ ማስቀጠል ላይ ትልቅ የቤት ስራ ይቀራል ። የህዝብ ለህዝብ ግንኙነቱ ላይ ቀጣይነት ያለውን ስራ መስራት የሚያስፈልገው። ከስር መሰረቱ በጥንቃቄ ተይዞ ለስኬት የሚበቃ የቤት ስራ፤ ሰላሙን በደንብ ለማጥበቅ መከናወን ያለበት ተግባር ነው ይላሉ።

መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ከጦርነቱ ድባብ ሞት፣ ስደት እና አካል መጉደልን ብቻ ነው ያተረፈው። በተለይ የጦርነቱ ቀጠና አካባቢ የነበረው ህብረተሰብ ወደ ሰላም መምጣቱና አሁንም የተገኘውን ሰላም መንከባከብ ተገቢ መሆኑን ይናገራሉ። ሰላሙንም ለማስቀጠል ሁሉም ማህበረሰብም ሆነ የመንግሰት አካላት እልህ እና ቂም በቀልን ወደ ጎን በመተው የሚያቀራርብ መልካም እሴት ላይ ትኩረት ማድረግ እንደሚገባቸው አብራርተዋል።

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል ኡስታዝ ካሚል ሸምሱ መንግሥት ለትግራይ ክልል የሚያደርገውን ተመሳሳይ የጦርነት ቀጠና በነበሩት አማራ ፣ አፋር አካባቢዎች ሰብዓዊ ድጋፎችን የሚያደርስበት እና የወደሙትንም መሰረተ ልማቶች መልሶ የሚገነባበት ሁኔታ ሊኖር ይገባል ብለዋል። ለአማራና ለአፋር ክልሎችም ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል ያሉት ኡስታዝ ካሚል ድጋፉን በአፋጣኝ እውን ለማድረግ ከዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ድጋፍ ለማግኘት ከሚደረገው እንቅስቃሴ በተጓዳኝ ክልሎችን በማስተባበር ያሉንን የውስጥ አቅሞች ለመጠቀም መጣር ወሳኝ መሆኑን ያስገነዝባሉ።

እንደ ኡስታዝ ካሚል ማብራሪያ፤ አንዳንድ የዓለም መንግሥታት እርዳታ ለመስጠት የሚያስቀምጡት ቅደመ ሁኔታ ተገቢ አይደለም። አሁን ላይ ከሁሉም የሚቀድመው ለተራበው ምግብ፣ ለተጠማው ውሃ፣ ለታመመው መድኃኒት፣ ጨለማ ውስጥ ላለው ደግሞ ብርሃን ማቅረብ ነው። አሁን የተጀመረው ግንኙነት ወደ ሕዝብ ወርዶ የነበረውን ወንድማዊ ፍቅርም ወደ ቦታው መመለስ እጅግ ጠቃሚ እንደሆነ ጠቁመዋል።

ቀድሞም በወንድማማችነት ተከባብሮ የሚኖረው ህብረተሰብ በቅድሚያ ሰብአዊነትን አስቀድሞ ህይወት የማትረፍ ተግባር ላይ ትኩረት ማድረግ እንደሚገባ የተናገሩት ኡስታዝ ካሚል ፤ ከዚህ በመቀጠል የፈረሰውን የህዝብ ለህዝብ የግንኙነት ድልድይን ጠግኖ በመቻቻልና በመከባበር ቀጣይነት ያለው ስራ መስራት ለዘላቂ ሰላም መፍትሄ መሆኑን ያስረዳሉ ።

እንደአስተያየት ሰጪዎቹ ገለፃ፤የሰላም ስምምነቱ መሬት እንዲረግጥ መንግስት በቁርጠኝነት እየሰራ ያለው ስራ ማሳያ ነው። በተደረሰው የሰላም ስምምነት መሰረት በቅድሚያ ሰብአዊ ድጋፍ ያለገደብ እንዲገባ፣ መሰረተ ልማቶች ስራ እንዲጀምሩ የተደረገበት ፈጣን እንቅስቃሴ እንዲሁም

ካለ ሶስተኛ ወገን የፌደራል መንግስት የልዑካን ቡድኑ ወደ መቀሌ ማቅናት የሰላም ስምምነቱ ወደ መሬት እየወረደ መሆኑን የሚያሳይ ነው። በአጠቃላይ የመንግስት ሰላም ወዳድነት የተገለፀበት ነው።

ማህበራዊ

# ሴቶች

## ሴቶችን ነጥሎ የማብቃት ጥረት - በእቴጌ መነን ትምህርት ቤት

ሰላማዊት ውቤ


ርዕሰ መምህርት ሀና ፀጋዬ


ተማሪ በዕምነት ኃይለማርያም


ተማሪ ሐኪማ ሲራጅ

በዕምነት ኃይለ ማርያም የ12ኛ ክፍል ተማሪ ስትሆን ወደ እቴጌ መነን አዳሪ ትምህርት ቤቱ የገባችው በ2012 ዓ•ም ነው። የመጣችው ደግሞ ከኮልፌ ቀራኒዮ መድሃኒዓለም 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው።ወደ ትምህርት ቤቱ መግባት የቻለችው በስምንተኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና 97 ነጥብ1 አምጥታ ነው።

በእምነት እንዳጫወተችን መግቢያ ፈተና ወስዳለች።ከተለያዩ ትምህርት ቤቶች ከመጡ ተማሪዎች ጋር ተፈትና ፈተናውን በአብላጫ ውጤት ካለፉት አንዷ በመሆኗ ነው ወደ እቴጌ መነን የሴቶች ትምህርት ቤት የገባችው። ከገባች በኋላ ከወንድ ተማሪዎች በአጠቃላይ ከማህበረሰቡ መነጠሉ እጅግ ከብዷት ነበር። ቀስ በቀስ ግን እየለመደችው ስትመጣ መነጠሉ ጠቃሚ መሆኑን ተገነዘበች።

ቤተ መጽሐፍት 24 ሰዓት ክፍት በመሆኑ መሸብኝ፤ወንዶች ይተነኩሱኛል፤ ቤት ያስባሉ ሳትል ባመቻት ጊዜ ትጠቀማለች።የተሟላም አይስቲ ክፍል ተገልጋይ አድርጓታል።በ12ኛ ክፍል ፈተና 625 አምጥታ ወደ ዩኒቨርስቲ በመግባት የሕግ ትምህርት የማጥናት ፍላጎቷን ለማሳካት የሚያስችላትን ዝግጅትም ከወዲሁ ማድረግ አስችሏታል።ምሳ፤ቁርስና ራት እንዲሁም አዳር እዛው በመሆኑ እንደ ፊቱ በምልልስ የምታባክነው ጊዜ የለምና በቂ የጥናት ጊዜም አግኝታለች።በትምህርት ቤቱ በሚካሄዱ የእግር ኳስና የተለያዩ ክበባትም ለመሳተፍ አስችሏታል።

ቀራኒዮ መድሃኒአለም ሁለተኛ ደረጃ በነበረችበት ጊዜ ለጥናት የማይመቹ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ነበሩ።በተለይ ሴቶች ሰብሰብ ብለውም ሆነ በግል ሲያጡኑ በወንድ ተማሪዎች በተደጋጋሚ ይረበሹ ነበር።ለነሱ ጨዋታ ቢመስላቸውም እሷን ያናድዳታል።ጎድቷታልም።

ለምሳሌበስምንተኛክፍልፈተና100አምጥታነበርወደ ዘጠነኛ ክፍል ማለፍ የፈለገችው። ሆኖም በነፃነት ማጥናት ባለመቻሏ ያሰበችውን ማምጣት አልቻለችም። በዕምነት እንደነገረችን ቤት ሆኖ መማርም ቢሆን ለሴት ተማሪ ውጤታማ የሚያደርግ ነው ብላ አታምንም።ምክንያቷን ስትገልጽም“ ‹‹ብዙ ጊዜ አብዛኞቹ ወላጆች የቤት ውስጥ ሥራ ሴቷ እንጂ ወንዱ ልጃቸው እንዲሰራ አይፈልጉም” ትላለች። እንዳከለችው ወንዱ ልጃቸው ውጭ፤ውጭ እንዲልና እንዲያጠናም ይፈልጋሉ።ኳስ እንዲጫወት ያደርጋሉ።ሴት ልጆቻቸው ግን በሥራ እንዲያግዟቸው ሲያደርጉ ነው የምታየው።በእርግጥ የእሷ ወላጆች እንደዚህ አይደሉም።የተሻለ ውጤት ማምጣትና አዳሪ ትምህርት ቤት ውስጥ መግባት የቻለችውም ለዚህ ነው።ሆኖም የሚኖሩት ለወንዶች በሚያዳላ ማህበረሰብ ውስጥ እንደመሆኑ ከተጽዕኖው ነፃ ናቸው ብላ አታስብም።

“እኔም ብሆን ምንም ያህል ጥናት ቢኖርብኝም እናቴ በሥራ ተወጥራ እያየሁ ቁጭ ብዬ ማጥናት አልችልም።እኔ እንኳን ዝም ብል ማህበረሰቡ “ሴት አይደለሽ አታግዢትም” ማለቱ አይቀርም”ብላናለች ተማሪ በዕምነት።ይሄ በተግባር እንደገጠማትም አክላልናለች።

ከወንዶች ተነጥሎ ሴቶች ብቻ የሚማሩበት ትምህርት ቤት መማር ሴት ተማሪዎችን ከነዚህ ሁሉ ተፅዕኖዎች ነፃ እንደሚያደርጋቸው የምትናገረው የ11ኛ ክፍሏ ተማሪ ሂከማ ሲራጅ ነች።ተማሪዋ እንደምትለው ወደ ትምህርት ቤቱ የመጣችው ሳሪስ 58 ቀበሌ ከሚገኘው መጋቢት 28 ትምህርት ቤት ነው።ዘንድሮ ሦስተኛ ዓመቷ ነው።“በቆይታዬ ደስተኛ ነበርኩ ብላለች።ምክንያቷ ከወንድ ተነጥሎና ከተፅዕኖ መራቅ መሆኑንም ትጠቅሳለች።

ከሚያስተምሯቸው መምህራኖች አብዛኞቹ ወንዶች መሆናቸውን እንዴት እንደምታየውም አንስተንላት ነበር።“መምህሮቻችን እንደ ልጆቻቸው ነው የሚያዩን።እኛም እንደ አባትና ወንድም ነው የምናያቸው” ብላናለች። ባላቸው ግንኙነት ችግር አላጋጠማቸውም እንጂ ከጾታዊ ጥቃትና ካልተገባ ግንኙነት ጋር ብቻም ሳይሆን ማንኛውም ችግር ሲገጥም የሚፈታበት ስርዓት መዘርጋቱንም ተማሪዋ ታወሳለች።ተማሪ ቤተሰብ እንዳይናፍቅ ወላጅ በፈለገው ጊዜ መጥቶ ያያቸዋል።እነሱም በየ15 ቀኑ ሄደው ወላጆቻቸውን ያያሉ።በዚህ ላይ ከጊቢው ማህበረሰብ ጋር ያላቸው መስተጋብርም ቤተሰባዊ በመሆኑ ብቸኝነት አይሰማቸውም።

በመሆኑም በዚህ መልኩ የሚቋቋም የሴቶች ዩኒቨርስቲ ቢኖር መልካም ነው ትላለች። ከወንዶች ጋር ተቀላቅሎ መማሩ በተለይም ከዕድሜ መድረስ አንፃር የአቻ ግፊት ስለሚያይል ለብቻቸው መማሩ ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡ በዚህ ደረጃ ሴቶች ለብቻቸው ዕውቀት እንዲጨብጡ ማድረግ ከራሳቸው አልፈው ለቤተሰብና ለአገር የሚተርፉ ብቁ ሴቶችን ለማውጣት ያስችላል የሚልም ዕምነት አላት።

“የአዳሪ ትምህርት ቤትና የዩኒቨርስቲ ባህርይ ተመሳሳይ ነው”ያሉን ደግሞ የሳይኮሎጂ መምህርቷ ወይንሸት ክብረት ናቸው። በመሆኑም ዩኒቨርስቲ ሲገቡ ብዙውን ስለተለማመዱት አዲስ አይሆንባቸውም ።ከዚህና ዕድሜያቸው እየጨመረ ሲመጣ ሊያጋጥማቸው ከሚችለው ተፅዕኖ ተጠብቀው እስከ መጨረሻው ውጤታማ እንዲሆኑ ለማስቻል በዩኒቨርስቲም ደረጃ ተነጥለው ቢማሩ የተሻለ ውጤታማ ይሆናሉብለው ያስባሉ። ብቃታቸውንና የሕይወት ክህሎታቸውን የሚያዳብሩበትን ጨምሮ በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ ተማሪዎቹን ያማክራሉ።የሚያማክሩት በግልም በቡድንም ወደ እሳቸው የሚመጡትን ነው።ማነቃቃት ላይም ይሰራሉ።

መምህር መስፍን ዘውዴ ቴክኒካል ድሮዊንግ ነው የሚያስተምሩት።መምህሩ እንደሚሉት ከወንዶች ተለይተው በተለይም አዳሪ ሆነው መማራቸው ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች አለው። ተለይተው በመማራቸው ከቤት ውስጥ ሥራ ጫና ነፃ ሆነዋል።ትምህርታቸውን በትኩረት እንዲከታተሉ ያስችላቸዋል።እሳቸው ወንድ ቢሆኑም ስለታጨበት መስፈርት እንዳያወጉን ጥያቄ አንስተንላቸው ነበር፡፡

‹‹ የተመለመሉት በዩኒቨርስቲ ባመጡት ከፍተኛ ነጥብና በሙያዩ ባለኝ የተሻለ አፈፃፀም ነው።በውጤታቸው መሰረት ከተመዘገብኩ በኋላ አዲስ አበባ ሜትሮፖሊታንት በዩኒቨርስቲ ያወጣውን መግቢያ ፈተና አለፍኩ።ስለዚህም ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ኃላፊነቱን ወሰድኩ ››ብለውናል፡፡

ካደግንበት ማህበረሰብ እንደምንገነዘበው ሴት ልጆች እዚህና ቤተሰብ መካከል ሆነው መማራቸው ልዩነት አለው። ቤት ሆነው ሲማሩ ሴት ሆና እናቷ ሥራ እየሰራች ዝም ብላ አታይም።ከጥናት ይልቅ እናቷን በሥራ ታግዛለች።እዚህ ግን ሥራ ስለሌለ ትኩረቷን በትምህርት ላይ ብቻ ነው የምታሳልፈው።ይሄ ደግሞ ውጤታማ ያደርጋታል። ሴቶች ከእናትነት ድርሻቸው ጀምሮ በሕብረተሰቡ ውስጥ የጎላ ሚና ያላቸው ከመሆናቸው አንፃር ከማንኛውም ጫና ነፃ ሆነው የሚማሩበት በመሆኑ እንደ መነን ያለው አዳሪ ትምህርት ቤት በመላ አገሪቱ ቢሰፋ የሚል ዕምነት አላቸው።

ለመምህሩ አንዳንድ ሰዎች ተነጥሎና በአዳር መማር ለሴቶች ካለው ጠቀሜታ አንፃር በዩኒቨርስቲ ደረጃም መስፋፋት አለበት የሚል ዕምነት ያላቸው መሆኑን አንስተንላቸው ነበር።እንደምላሻቸው ታድያ አሁን ላይ በአዳር የምንቀበላቸው ህፃናት ናቸው።ዕውቀት መጨበጥና መያዝ የሚችሉትም በዚህ ዕድሜ ነው።ከዚህ ከሚያስተጓጉላቸው የቤት ውስጥ የሥራ ጫናና ሌሎች ተጽዕኖዎች ነፃ መሆን ያለባቸውም አሁን ነው። ዩኒቨርስቲ በሚገቡበት ጊዜ ያድጋሉ።በዕድሜም ይበስላሉ።ክፉና ደጉን ስለሚለዩና ለከፍተኛ ትምህርት መሰረት የሚሆናቸውን ዕውቀትም ቀድመው ስለሚይዙ በትምህርታቸው ለመጠንከርም ሆነ የአቻ ግፊትና ሌሎች ተፅዕኖዎችን ለመቋቋም ይችላሉ።በዚህ ላይ ዩኒቨርስቲ በባህሪው ከነበሩበት ከአዳሪ ትምህርት ቤት ጋር የሚመሳሰልና ከቤት ውስጥ የሥራ ጫና የሚያላቅቅ በመሆኑ ተነጥለው መማራቸው አስፈላጊ ነው ብለው አያምኑም። ተቀላቅለው ቢማሩ በጋራ ለመኖር አስፈላጊ ጉዳዮችን እየተገነዘቡ ወደ ማህበረሰቡ ውስጥ መግባት ይችላሉ ይላሉ።

የትምህርት ቤቱ ዋና ርዕሰ መምህርት ሀና ፀጋዬም ሴቶች ተነጥለው በአዳሪነት መማራቸው የጎላ ጥቅም እንዳለው ነው በአፅዕኖት የሚናገሩት።‹‹እንደ ሴትም ሳየው ሴቶች ከወንድ ተነጥለው ብቻቸውን መማራቸው በጣም ጥሩ ነው›› ይላሉ ።እንደ እሳቸው ብዙ ጊዜ ሴቶች ብቻቸውን ተነጥለው መማራቸው በተለያየ መልኩ ችግር ያመጣባቸዋልና ማህበራዊ መስተጋብራቸውን ያላላል የሚሉ አንዳንድ ሰዎች አሉ።ሆኖም ከአንድ እስከ ስምንተኛ ክፍል ሲማሩ ከወንድ ተማሪዎች ጋር አብረው ነው የተማሩት። ወደ ዩኒቨርስቲም ሆነ ወደ ቤታቸው ሲሄዱም ከወንድሞቻቸው ጋር ይቀላቀላሉ። በተጨማሪም በእቴጌ መነን የሴቶች ትምህርት ቤት ውስጥ ካሉት 56 መምህራን መካከል 44ቱ ወንዶች ናቸው።ምንም የተለየ ነገር አይኖረውም ።እንደውም እርስ በእርስ ለመረዳዳት ያለባቸውን የቤት ውስጥ የሥራ ጫና ፤የቤተሰብ ተፅዕኖ ለመቅረፍ ፤በምግብ ፤መኖሪያ በማጣት፤ ዘመድ ጋር ተጠልለው ነጥብ አምጥተው የሚያስተምሯቸውንና የሥራ ጫና የሚበዛባቸውን ሥራ የሚያሰሯቸው ወላጆች ሁሉ ያሉበት ችግር ተማሪዎች እዚህ ትምህርት ቤት ገብተው በመማራቸው ይቀረፍላቸዋል። እኛ ባደረግነው ጥናት ማደሪያ የሌላቸው እና ነጥብ ያመጡ ሴቶች ስላሉ ትምህርት ቤቱ አዳሪ መሆኑ ጠቅሟቸዋልም ነው የሚሉት። አዳሪ ሆነው በመማራቸው በተግባርም የተሻለ ውጤት ሲያመጡ እየታየ ነው።እውነታው ጥናት ተደርጎ ተረጋግጧል። እንደ ትምህርት ሚኒስቴርም እንደዚህ ዓይነት አዳሪ ትምህርት ቤትን ለመክፈት ይቻል ዘንድ ከትምህርት ቤቱ ተሞክሮ ተወስዷል።

በተጨማሪም ልጃገረዶቹ እንደሌሎቹ ተማሪዎች በመጓጓዝ የሚያባክኑት ጊዜ የለም።የምልልሱ ጊዜ ማጠሩ በራሱ ለጥናት፤ለሌሎች የቤትና የክፍል ሥራዎቻቸው የሚያደርገው እገዛ የላቀ ነው። በዛ ላይ ምግብና መጠለያ እየተቸገሩ ይማሩ የነበሩ ጠንካራ ተማሪዎችም ወደ ትምህርት ቤቱ የገቡ በመሆናቸው ቁርስ፤ምሳና እራት መዘጋጀቱ እንዲሁም አዳር መሆኑ በፊት ይቸገሩበት የነበረውን ሁኔታ በማስቀረት ትኩረታቸው ትምህርት ላይ ብቻ እንዲሆን ያደርጋል።በትምህርት ውጤታማ ለማድረግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው።በዚህ ላይ ተማሪዎቹ ወደ ትምህርት ቤቱ የሚመጡት ቦርሳና ደብተራቸውን ብቻ ይዘው ነው። አንሶላና ትራስን ጨምሮ ብርድ ልብስና ፍራሽ የሚያቀርብላቸው ትምህርት ቤቱ ነው። ተደራራቢ አልጋም እንዲሁ ትምህርት ቤቱ ነው የሚያዘጋጅላቸው ።

በጠባቧ መኝታ ክፍል ስድስት ፤በሰፊው ደግሞ 12 ተማሪዎች ሆነው በተደራራቢው አልጋ ላይ በተናጠል ይተኛሉ። ክፍሉም ሆነ መኝታው በጋራም ሆነ በግል ለማጥናት ጭምር እንዲያመቻቸው ተደርጎ ነው የተዘጋጀው።ደህንነቱም ቢሆን የተጠበቀ ነው።በተጨማሪም ይሄን ለማረጋገጥ ትምህርት ቤቱ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል።ከመምህራን ጋር ያላቸው ግንኑነት ችግር አለው የለውም በሚል ይፈትሻል። መምህራኖቹ ሲመረጡ የስነ ምግባር ችግር እንደሌለባቸው ተረጋግጦ ሌላ ትምህርት ቤት የተሻሉ ተብለው ነው የመጡት።መምህራኑ ወደ ትምህርት ቤቱ ከመጡ በኋላ በየጊዜው እየተፈተሸ ይሄዳሉ፡፡

አስፈላጊ ቁሳቁሶችን ከሚያቀርቡላቸውና ክፍላቸውን ከሚያፀዱላቸው ሴት ፅዳት ሠራተኞች በስተቀር ወደ መኝታ ክፍላቸው የሚሄድ የለም።ትምህርቱና ቆይታቸው አዳር በመሆኑና መጓጓዝ ስለሌለባቸው የበለጠ ደህንነት ይሰማቸዋል።ከለከፉ ጀምሮ መንገድ ላይ የሚገጥሙ መሰናክሎችንም ያስቀርላቸዋል።ርዕሰ መምህርቷ ከጤና ጋር ተያይዞ ሊገጥማቸው የሚችለውን ከመፍታት አንፃር በትምህርት ቤቱ ያለውንም ሲናገሩ ከእንጦጦ ጤና ጣቢያ እና ከየካቲት 12 ሆስፒታል ጋር ትምህርት ቤቱ ባደረገው ትስስር በሚያማቸው ወቅት ይታከማሉ።መድሃኒት ይታዘዝላቸዋል። የተማሪዎቹ የሕክምና ወጪ ሙሉ በሙሉም ይሸፈናል።በወር ወይም በ15 ቀን አንድ ቀን ከትምህርቱ ጋር በማይጋጭ ሁኔታ ቤተሰባቸውን ጠይቀው እንዲመጡም ይደረጋል። ቀደም ሲል አንዳንድ ወላጆች ልጆቻቸው በትምህርት ቤታችን አዳሪ ሆነው በመማራቸው ብዙም ደስተኛ አልነበሩም።ሆኖም ልጆቻቸው ውጤታማ እየሆኑ ሲመጡ ፤ጥቅሙን ሲያዩት፤ልጆቻቸውም እየወደዱት ሲመጡ ደስተኛ መሆን ችለዋል ይላሉም ርዕሰ መምርቷ ሀና ፀጋዬ።

በትምህርት ቤቱ እሳቸውን ጨምሮ አራት ርዕሰ መምህራን ሲኖሩ ሦስቱ የአካዳሚ ዘርፉን፤የተማሪዎች ምግብ መኝታቸውን የሚቆጣጠሩ ናቸው። የተማሪዎችም ዲን አለ።ፋይናንስ፤የሰው ኃይልና ሌሎችን የምታስኬድ ሴት ርዕሰ መምህርት አለች።በድምሩ 114 ሠራተኞች አሉ።ከነዚህ መካከል 56ቱ መምህራን ሲሆኑ ሌሎቹ ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ናቸው።ከ56ቱ መምህራን መካከልም 44ቱ ወንዶች ናቸው። ወንዶቹ መምህራን ከተማሪዎቹ ጋር ያላቸው ግንኙነት ቤተሰባዊ ነውም ይላሉ።

የእቴጌ መነን የልጃገረዶች አዳሪ ትምህርት ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ብቸኛው የመንግስት ትምህርት ቤት ነው።በየዓመቱ 500 ተማሪዎችን ይቀበላል።ትምህርት ቤቱ እያስተማረ የሚገኘው ከዘጠነኛ እስከ 12ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎችን ነው። ተማሪዎቹ አዲስ አበባ ከሚገኙ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ተውጣጥተው የመጡ ሲሆኑ የስምንተኛ ክፍል መልቀቂያ ወስደው ከ75ና በላይ ያመጡ ናቸው።

ትምህርት ቤቱ በ2012 ዓ.ም ትምህርት ሲጀምር የተቀበላቸው ልጃገረድ ተማሪዎች 300 ሲሆኑ የ11ኛ እና የ12ኛ ጥቂት ተማሪዎችንም ይዞ ነበር።ዘንድሮ ከተቀበላቸው 500 ተማሪዎች መካከል ሰባቱ ጠይቀው አዳማ አዳሪ ትምህርት ቤት ስለሄዱ 493ቱን እያስተማረ ይገኛል።ከነዚህ ውስጥም 177ቱ በዚህ ዓመት መጨረሻ የሚሰጠውን የ12ኛ ክፍል አገር አቀፍ ፈተና የሚወስዱና በከፍተኛ ዝግጅት ላይ የሚገኙ ናቸው።

የቅበላ አቅሙን በየዓመቱ እየጎለበተ ሄዶም ዘንድሮ 500 ተማሪዎችን ተቀብሎ ማስተማር ደረጃ ላይ ደርሷል። ቁጥሩ እየጨመረ የመጣው የመኝታው፤ የምግቡና ሌላው አገልግሎት እየሰፋ በመሄዱ ሲሆን የቅበላ አቅሙ ከ500 በላይ ስለማይፈቅድም ከፍተኛ ነጥብ ያመጡና ለመግባት የተመለመሉ በርካታ ሴት ተማሪዎች ቢኖሩም ለማስተናገድ አልቻለም።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

ሙሉጌታ ብርሃኑ

አዲስ ዘመን ድሮ እንዴትና ምን ይመስል ነበር? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ በዛሬው የአዲስ ዘመን ድሮ አምዳችን ትኩረታችንን በ60ዎቹና በ70ዎቹ በጋዜጣው የወጡ ዜናዎች ላይ አድርጓል። አንዳንዶቹ ፈገግታን የሚያጭሩ ቢሆኑም ጋዜጣው ምን ያህል ለማህበረሰቡ ቅርብ እንደነበረም የሚያመላክቱ ናቸው። ሲጃራ ተደብቆ ያጨሰው ግለሰብ ለፍርድ መቅረብ፣ ማንበብና መጻፍ የሚችሉ ጥቂት አዋቂዎች በነበሩበት ዘመን ማንበብና መጻፍ ስለቻለችው አስገራሚዋ የአራት አመት ህጻን፣በሞስኮ አሎምፒክ ለሀገሩና ለአህጉሩ የመጀመሪያውን የወርቅ ሜዳሊያ ስላስገኘው ጀግና አትሌት፣ስለመጀመሪያው የሳታላይት ጣቢያ መከፈት እና ሰዎች ሲሞቱ ስለዳነው እንስራ እንዲሁም ከህብረተሰቡ ውስጥ ከሚላኩት ደብዳቤዎች መሃከል ሁለቱን ለትውስታ ያህል አካተን አቅርበንላችኋል።

**ሲጃራ ተደብቆ ያጨሰው ተከሰሰ**

ከሲጃራ ፋብሪካ ውስጥ ሰራተኛ ሆኖ ሳይፈቀድለት ከሽንት ቤት ውስጥ ተደብቆ ሲያጨስ የተገኘው በልሁ ተሰማ ተከሶ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቀረበ።

ተከሳሹ የካቲት ፲፫ ቀን ፩፱፻፷፪ዓ.ም ከፍተኛ ፍርድ ቤት 3ኛ ወንጀል ችሎት በቀረበ ጊዜ ያለመስሪያ ቤቱ ፈቃድ 5 ሲጋራዎች ተደብቆ ማጨሱን አምኗል።

የቀረበበት የአቃቤ ሕግ ክስ እንደሚያመለክተው ከሆነ ተከሳሹ ከአዲስ አበባ ትምባሆ ፋብሪካ ወስዷል የተባለው የሲጃራ ፓኬት በርከት ያለ መሆኑን ያመለክታል። ጉዳዩ እስኪጣራ ተከሳሹ በ፵፪ ብር ዋስትና እንዲለቀቅ ፍርድ ቤቱ አዟል። (ህዳር 9/1962ዓ.ም)

**የአራት አመት ሕጻን ማንበብና መጻፍ ቻለች**

ጅማ፣(ኢ-ዜ-አ) ካለፈው ግንቦት ወር ጀምሮ በከፋ ክፍለ ሀገር በመካሄድ ላይ በሚገኘው በሦስተኛው ዙር የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ ትምህርት በመቀበል እጅግ ፈጣንና ብሩህ አእምሮ ያላት የአራት አመት ልጅ ተገኘች።

በጅማ አውራጃ በቀርሳ ወረዳ በኩሳዬ ቡሬ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ውስጥ ነዋሪ ከሆኑ ገበሬ ቤተሰብ የተወለደችው ራውዳ አባቦር የተባለችው ይህችው ሕጻን ፈጣንና ብሩህ አእምሮ ያላት መሆኑን የታወቀው በአከባቢው በተከፈተው የመሰረተ ትምህርት መስጪያ ጣቢያ በመሄድ ከእናቷ ጋር ተቀምጣ በመማር በሁለት ወር ውስጥ የፊደልን ዘር ለይታ መጻፍና ማንበብ በመቻሏ ነው። (ነሀሴ 7/1972ዓ.ም)

**ሊቀመንበሩ ሳተላይት ጣቢያ መርቀው ከፈቱ**

አዲስ አበባ፣(ኢ-ዜ-አ) ጓድ ሊቀመንበር መንግስቱ ኃ/ማርያም የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ሊቀመንበር የሚንስትሮች ምክር ቤት ሰብሳቢና የአብዮታዊ ጦር ጠቅላይ አዛዥ ከትላንት በስቲያ በመናገሻ አውራጃ በሱሉልታ ወረዳ በ14 ሚሊዮን 72 ሺህ ብር ወጪ የተሰራውን የሳተላይት የምድር መገናኛ ጣቢያ መርቀው ከፍተዋል። (ሰኔ 14/1972ዓ.ም)

**ጎመንና ቅቤ ሰርቆ 18 ወር ታሰረ**

በእምነት ከቤት እንዲያደርስ የተሰጠውን ጎመንና ቅቤ ለግል ጥቅሙ ያዋለው ዓለሙ ዋጭላ ተከሶ በ ፲፰ወር እስራት ተቀጣ።

ዓለሙ ታህሳስ ፳፪ ቀን ፩፱፻፷፩ዓ.ም ከቀኑ 6 ሰዓት ላይ የእመት አሚና ጂቢሊን ቅቤና ጎመን ይዞ መጥፋቱንና በፖሊስ መያዙ ታውቋል። አዲስ አበባ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቀርቦ ቅጣቱንም ተቀብሏል። (ሰኔ 10/1972ዓ.ም)

**ሰዎች ሲሞቱ እንስራው ዳነ**

ቁጥሩ 647 የሆነ ሴይቼንቶ ኅዳር ፬ ቀን ፩፱፻፷፩ዓ.ም ከቀኑ 9 ሰዓት ላይ ስድስት ሰዎች አሳፍሮ ከአዲስ አበባ ወደ አለም ጤና ሲጓዝ ከሞጆ አቅራቢያ ካለው ድልድይ በስተግራ በኩል የመገልበጥ አደጋ ደርሶበታል።

በዚሁ መኪና ውስጥ ተሳፍረው ከነበሩት ስድስት ሰዎች ውስጥ ሁለቱ ወዲያውኑ ሲሞቱ ሁለቱ ደግሞ ከፋኛ የመቁሰል አደጋ ደርሶባቸዋል። እንዲሁ ሁለቱ ቀላል መቁሰል አደጋ እንደደረሰባቸው የሸዋ ፖሊስ ትራፊክ ክፍል ገልጦአል።

በዚሁ አደጋ ወቅት የመኪናው ባለቤትና ሾፌሩ ያልተገኙ መሆናቸው ታውቋል። በመኪና ውስጥ ባሉት ሰዎች ላይ አደጋ ሲደርስ ተጭኖ በነበረው እንስራ ላይ ግን ምንም ጉዳት ያልደረሰበት ሆኖ መገኘቱን የትራፊክ ክፍሉ በድጋሚ አስረድቷል። (ህዳር 10/1962ዓ.ም)

በሞስኮ አሊምፒክ ኢትዮጵያ የወርቅ ሜዳሊያ ለማግኘት የመጀመሪያዋ የአፍሪካ ሀገር ሆነች

በሶቪየት ህብረት ሞስኮ ከተማ በመካሄድ ላይ ባለው የ፳፪ኛው የኦሎምፒክ ውድድር የ፲ሺህ ፍጻሜ ባለፈው እሑድ ተደርጎ ጀግናው አትሌት ሻምበል ምሩፅ ይፍጠር አንደኛ በመውጣት ለአብዮታዊት ኢትዮጵያና ለአፍሪካ አህጉርም ጭምር የመጀመሪያውን የወርቅ ሜዳሊያ አስገኝቷል።(ሀምሌ 22/1972ዓ.ም)

**ከደብዳቤዎች**

**“ወንበሩ የኔ አይደለም”**

‘ወንበሩ የኔ አይደለም ባለወንበሯን እዘዝ’ የሚሉ ቃላት በአሁኑ ጊዜ በየቡና ቤት ሰራተኞች ተዘውትረው ይነገራሉ።

ይህንን ደብዳቤ ለመጻፍ ያነሳሳኝ በ፲፩ -፲ -፷፪ ዓ/ም ከምሽቱ ሁለት ሰዓት መርካቶ ውስጥ በሚገኘው አዲስ ከተማ ቡና ቤት ውስጥ ቡና አዝዤ ቀርቦልኝ ስኳር በማነሱ አንዷን የቡና ቤቱ ሰራተኛ ስኳር እንድትጨምርልኝ ብጠይቃት ‘ወንበሩ የኔ አይደለም ባለ ወንበሯን እዘዝ’፣ የሚል መልስ ሰጠችኝ። እንግዳን ማስተናገድ ለድርጅቱ ዕድገት ጠቃሚ ከመሆኑም በላይ በዚሁ አንጻር የሠራተኞችም ኑሮ ሊያድግ ስለሚችል ተባብሮ መስራት የሚሻል መሆኑ አይጠረጠርም። ይህ ካልሆነ ግን ድርጅቱ ብቻ ሳይሆን፣ በራስ ላይም ውድቀት ሊያስከትል ይችላልና ይታሰብበት።

ልሳነወርቅ አስፋው

ከፍተኛ 5 አዲስ አበባ

ሰኔ 15/1972ዓ.ም

**ጥንቃቄ ይደረግ**

ቅዳሜ ሰኔ ፳፰ ቀን ፩፱፻፷፪ዓ.ም ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ገደማ በአዲስ ከተማና በተክለሃይማኖት አከባቢ በጣለው ዝናብ በከፍተኛ ፫ ቀበሌ ፴፩ ክልል ውስጥ አንዳንድ አሮጌ ቤቶች በጎርፍ ተሞልተው ነበር። ነዋሪዎችም እቃዎቻቸውን ከጎርፍ ብልሽት ለማትረፍ ቢጥሩም ብዙ ዕቃዎች መበላሸታቸውን ተመልክቻለሁ።

በዚያ ቀበሌ በርከት ያሉ አሮጌ ቤቶች ስለአሉ አሁንም የነዋሪዎች ንብረት እንዳይበላሽ ጥንቃቄ ይደረግ።

ወታደር ተዘራ አስፋው

ነሀሴ 9/1971ዓ.ም

# ዓለም አቀፍ

## ኒው ዮርክ የሰዎችን አስክሬን በፋብሪካ ወደ ብስባሽ አፈር መቀየር ልትጀምር ነው

ኒው ዮርክ የሰው ልጅን አስክሬን ወደ ብስባሽ አፈር መቀየር የሚፈቅድ ሕግ አጸደቀች።ይህን ተከትሎ ሰዎች ሲሞቱ አስክሬናቸው ወደ ብስባሽ አፈርነት እንዲቀየር መናዘዝ ይችላሉ።አስክሬንን በሳጥን አኑሮ ግብዓተ መሬቱን መፈጸም ወይም ሬሳን ማቃጠል ለአካባቢ ጥበቃ መልካም አይደለም ይላሉ ተመራማሪዎች።

ይህን ችግር ለመቅረፍ አዲስና ዘመናዊ የሬሳ ማስወገጃ ሥራ ተግባር ላይ ማዋል አስፈልጓል።በእንግሊዝኛው ናቹራል ኦርጋኒክ ሪዳክሽን (“natural organic reduction”) የሚባለውና አስክሬንን ወደ ብስባሽ አፈር የሚቀይረው ይህ ዘመናዊ ሂደት ሬሳዎችን አሸጎ በማቆየት የሚፈጸም አካባቢን የማይበክል ሂደት ነው ይላሉ ተመራማሪዎች።

ከአራት ዓመት በፊት ዋሽንግተን ተመሳሳይ ደንብን ሕግ አድርጋ አጽድቃ እንደነበር ይታወሳል።ኮሎራዶ፣ ኦሪገን፣ ቬርሞንት እና ካሊፎርኒያ ዋሽንግተንን ተከትለው ይህንን ሕግ አጽድቀዋል።ኒው ዮርክ አስክሬንን ወደ ብስባሽ አፈርነት መቀየር የሚፈቅድ



ሕግ ስታጸድቅ ስድስተኛዋ የአሜሪካ ግዛት ናት።ይህን ረቂቅ የኒው ዮርክ ገዥ የሆኑት ዲሞክራቷ ካቲ ሆኩል ሕግ እንዲሆን ፈርመውበታል።

ይህ ሬሳን ወደ ብስባሽ የሚቀይረው ሳይንስ ከመሬት ከፍ ብሎ በሚቀመጥ የሳጥን በርሜል የሚፈጸም ነው።አስክሬኖች ዝግ በሆነ በርሜል መሰል ማስቀመጫ ከተጋደሙ በኋላ የእንጨት ፍቅፋቂ፣ ሳር፣ አፈር እና ሌሎች ንጥረ ነገሮች ይርከፈከፉባቸዋል። ከዚያ አስክሬን አብሮ ይቀየጣል።ማንኛውም ተላላፊ በሽታ እንዳይኖር ከፍ ያለ ሙቀት ይደረግበታል።

ከአንድ ወር በኋላ ብስባሽ አፈር ሆኖ ለቤተሰብ ይሰጣል። ቤተሰብ ይህን አፈር ተቀብሎ ለጓሮ አትክልት ሊያውለው ይችላል።ሪኮምፖስ የሚባል አንድ የአሜሪካ ኩባንያ እንደሚለው ይህ ሂደት የካርበን ልቀትንበብዙደረጃቀንሶየአካባቢብክለትንየሚከላከል ሁነኛ ዘዴ ሲል አሞካሽቶታል።የካርቦንዳይኦክሳይድ ልቀት ለዓለም አየር ንብረት መለወጥ አንድ ሁነኛ ምክንያት ነው።

ይህም የመሬትን ከባቢ በማፈን ሙቀትን ስለሚፈጥር ነው።ባሕላዊው ሬሳን የመቅበሪያ ዘዴ በርካታ ሳጥን መፈለጉና ለዚህም ሲባል በርካታ የደን ምንጣሮ ስለሚያስፈልግ ነው።ከምንጣሮ ሌላ መካነ መቃብርም በርካታ ቦታ ይይዛል። በከተሞች አካባቢ ይህ ትልቅ ፈተና ሆኗል።የዚህ ሬሳን ወደ ብስባሽ አፈርነት የመቀየር ሂደት ደጋፊ የሆኑ ባለሙያዎች እንደሚሉት ይህ ዘዴ በተለይ መሬት ውድ ለሆነባቸው የዓለም ከተሞች ሁነኛ መፍትሄ ነው።

በተቃራኒው ሌሎች የሞራል ጥያቄን ያነሳሉ።የኒው ዮርክ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ቄስ “የሰው ልጅ ክቡር ነው፤ አስክሬኑ እንደቆሻሻ ብስባሽ አይደረግም፤ ነውር ነው’ ሲሉ ተቃውሟቸውን አሰምተዋል።ይህን ሬሳን ብስባሽ የማድረግ ሂደት ከተለመደው ቀብር የማስፈጸሚያ በዋጋ አነስተኛ ቢሆንም እስከ 7ሺህ ዶላር ወጪ ያስወጣል።የሰውን አስክሬን ወደ ብስባሽ አፈር የመቀየር ሂደት በስዊድን ሕጋዊ ነው።በዩኬ ደግሞ አስክሬንን ያለ ሬሳ ሳጥን መቅበር ይፈቀዳል ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።

## አዲሱ የብራዚል ፕሬዝዳንት አገራቸውን ወደ አረንጓዴ ልዕለ ኃያልነት እቀይራለሁ አሉ

ሉዊዝ ኢናሲዮ ሉላ ዳ ሲልቫ እሁድ እለት የብራዚል ፕሬዝዳንት ሆነው ቃለ-መሃላ ሲፈጽሙ ብራዚልን ወደ አረንጓዴ ልዕለ ኃያልነት እንደሚለውጡ ገልጸዋል።አዲሱ ፕሬዝዳንት በቀድሞው መሪ ጃየር ቦልሶናሮ ላይ ከባድ ክስ በማቅረብ በረሀብ ፣ በድህነት እና በዘረኝነት የተመሰቃቀለውን ህዝብ ለመታደግ ከባድ ለውጥ ለማድረግ ቃል ገብተዋል ።ሉላ የላቲን አሜሪካዋን ትልቅ ሀገር ለመምራት በይፋ ስልጣን ከያዙ በኋላ ለምክር ቤቱ ባደረጉት ንግግር፤ የጥቅምቱ ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ እውነተኛ አሸናፊ ዲሞክራሲ ነው ብለዋል።

ሽንፈቱን ለመቀበል አሻፈረኝ ሲሉ የከረሙት ቦልሴናሮ አርብ እለት ብራዚልን ለቀው አሜሪካ ገብተዋል።ሉላ ቦልሶናሮን በስም ሳይጠቅሱ “ሀገሪቷን ለግል እና ርዕዮተ-ዓለማዊ ጥቅም ለመግዛት በሞከሩት ላይ ምንም አይነት የበቀል መንፈስ አንይዝም፤ ነገር ግን የህግ የበላይነትን እናረጋግጣለን” ብለዋል። “እነዚያ የተሳሳቱ ሰዎች ለኃጢአታቸው መልስ ይሰጣሉ” ሲሉም ገልጸዋል።

በተጨማሪም ከ680 ሺህ በላይ ብራዚላውያንን ለገደለው የኮቪድ-19 ቫይረስ ተገቢውን ምላሽ ባለመስጠት የቦልሶናሮ አስተዳደር “ዘር ማጥፋት” ፈጽሟል ሲሉ ከሰዋል።”ለዚህ የዘር ማጥፋት ወንጀል ኃላፊነቱ ይጣራል። ከቅጣት ነጻ መሆን አይቻልም” ነው ያሉት።

ምንምእንኳንየቦልሶናሮየፍሎሪዳጉዞበብራዚል ውስጥ ካሉ ከማንኛውም የህግ አደጋዎች የሚከላከል ቢሆንም፤ ከጸረ-ዲሞክራሲያዊ ንግግራቸው እና ከወረርሽኙ አያያዝ ጋር በተያያዘ የፕሬዝዳንትነት ያለመከሰስ መብታቸውን ካጡ በኋላ የመከሰስ አደጋ ተጋርጦባቸዋል ተብሏል።የሉላ የመንግስት እቅድ ከቦልሶናሮ የአራት ዓመታት የስልጣን ዘመን ጋር ፍጹም ይለያል መባሉን ሮይተርስ ዘግቧል።



ሉላ ከዓለም ከፍተኛ የምግብ አምራቾች መካከል አንዷ የሆነችውን ብራዚልን ወደ አረንጓዴ ልዕለ ኃያልነት መለወጥ እንደሚፈልጉ መናገራቸውን አልዐይን ዘግቧል።

## የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ

በፍርድ ባለመብት ህብር አግሮ ኢንዱስትሪ ኩባንያ ኃላፊነቱ የተ/የግ/ማህበር እና በፍርድ ባለዕዳ ባስኬት ና ድችስቶ ኃ/የተ/ሁ/የገ/ህብረት ሥራ ዩኒየን መካከል ባለው የፍርድ አፈጻፀም ክርክር የፍርድ ባለዕዳ ንብረት የሆኑት 1.የንግድ ድርጅት ቤት በላስካ ከተማ 02 ቀበሌ ኦቾ ሰፈር፣የቦታ ስፋት 772.62 ካሬ ሜትር ላይ ያረፈ አዋሳኞቹ በሰሜን መንገድ፣በደቡብ አቶ ታርኩ በለጠ፣በምዕራብ አቶ ጌታሁን ለማ እና በምስራቅ መንገድ የሆነው የንግድ ድርጅት ቤት በመነሻ ዋጋ ብር 2,000,000(ሁለት ሚልዬን) 2.የባለዕዳው አይሱዚ የጭነት መኪና ታርጋ ቁጥሩ A03-A21946 ሞዴሉ 215 ቻንሲ ቁጥር JAAKPK34HXF7P18202፣ሞተር ቁጥር 4HG1350279,,ያገለገለበት በኪሎ ሜትር 180,000 አሁን ያለበት ደረጃ ጉልበት _ 67% መነሻ ዋጋ 1,600,000 ብር(አንድ ሚሊዬን ስድስት መቶ ሺህ) የሆኑት ንብረቶች የካቲት 1/2015 ዓ/ም ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ላይ በግልጽ ሐራጅ ይሸጣሉ፡፡ በመሆኑም ለመጫረት የሚፈልግ ማንኛውም ተጫራች ማስታወቂያው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከታተመበት ቀን ከ1ወር በኃላ የያንዳንዱን ንብረት የመነሻ ዋጋ ግምት 1/4ኛ በማስያዝ ባስኬቶ ከፍተኛ ፍ/ቤት ቢሮ ቁጥር 7 ቀርቦ መጫረት የሚችል መሆኑን ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**በደ/ብ/ብ/ክ/መ/የባስኬቶ ልዩ ወረዳ ከፍተኛ ፍ/ቤት መ/መ የስራ ሂደት**

## INVITATION TO BID
## Bid NO. NCB/GOV/AAWSA/W004/2022

1. Addis Ababa water and sewerage Authority invites interested contractors (Water Well Driling/ Water Works Contractor/ General Contractor Grade Three (3) and above) to participate for the Construction of Water Well Rehabilitation, Development & Pumping Test Works.
2. The bid documents shall be purchased from the Procurement Support Process during office hours against payment of non-refundable fee of Birr 700.00 (Birr Seven Hundred).
3. The bid shall be submitted in two separate envelops: 1. Technical envelop 2. Financial envelop. One original and one copy each.
4. Interested eligible bidders may obtain further information at the office of A.A.W.S.A Procurement Support Process Located at Megenagna, next to Ministry of Revenue Head Office, on the road to old 24 Kebele, P.O.BOX 1505, Addis Ababa, Ethiopia, and Tel.+251 116630857/+251 11 662 00 10 Fax; -+2510116623924. The bid must be accompanied by a bid security of For Lot one Birr 100,000.00 (Birr One Hundred Thousand) and For Lot Two Birr 150,000.00 (Birr One Hundred Fifty Thousand) in the form of unconditional bank guarantee, conditional insurance guarantee, and certified payment order (C.P.O) or cash. The bid Security shall be valid for at least 90 days & should be in a separate envelope submitted in the tender box together with the bid documents.
5. The winner contractor shall furnish 10% of the contract amount as performance security within 15 days as of the contract signing date.
6. All eligibility certificates should be found in the original technical envelop.
7. The bid must be deposited in the tender box prepared for this purpose at or before 2:00 P.M. and shall be opened at 2:30 P.M. on January 24, 2023 G.C. in the presence of bidders and/or their official representatives who wish to attend.
8. The Authority reserves the right to accept or reject the bid partially or wholly.

**ADDIS ABABA WATER & SEWERAGE AUTHORITY**
**Address: Megnagna, next to Ministry of Revenue Head Office on the road to old 24 Kebele, P.O.BOX 1505, Addis Ababa, Ethiopia, and Tel +251-116-63 08 57/+25111662 00 10**
**Addis Ababa water and sewerage Authority**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

የባለንብረት ስም ሜድሮክ ኢትዮጵያ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-02699 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር XLBKC103EVC759140 ሞዴል 4401.81 የሞተር ቁጥር B18U-200-1122709 የሊብሬ ቁጥር 260717 ከላይ የተጠቀሰው የተሽርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው 18/4/2015አመልክተዋል። የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ 015 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገኛ ትዕዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን ቦሌ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ነበሩ አንባው ወንድምአለኝ የሰሌዳ ቁጥር አአ 02-01-B64663 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር SCP10-5011558 ሞዴል GH-SCP10AHPEK የሞተር ቁጥር 1SZ-0364090 የሊብሬ ቁጥር 239685 ከላይ የተጠቀሰው የተሽርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው 20/4/2015 አመልክተዋል።
የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገኛ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን ለሚ ኩራ ቅ/ጽ/ቤት**

## የንግድ ምልክት ዕድሳት ማስታወቂያ

| | | |
|---|---|---|
| 1 | የባለቤቱ ስምና አድራሻ | ቤክተን ዲክሰን ኤንድ ካምፓኒ (Becton, Dickinson and Company)<br>1 Becton Drive, Franklin Lakes, New Jersey 07417,U.S.A |
| 2 | የማመልከቻ ቁጥር | FTM/6723/2015 |
| 3 | የዕድሳት ጊዜ | ከ06/10/2022 እስከ 06/10/2029 |
| 4 | የንግድ ምልክቱ | **BD VACUTAINER ULTRATOUCH** |
| 5 | ባለቤቱ ይህንን የንግድ ምልክት የሚጠቀመው በዓለምአቀፍ ምድብ 10 በ07/09/2010ዓ.ም. በአዲስ ዘመን ጋዜጣ Vol.LXXVII No.247 በወጣው ማስታወቂያ ከተዘረዘሩት ምርቶች ጋር በተያያዘ ነው፡፡ | |
| 6 | . ማንኛውም ግለሰብ ወይም ሕጋዊ ሰውነት ያለው ተቋም ከባለቤቱ ሳያስፈቅድ በዚህ የንግድ ምልክት በሚገለገል ወይም አስመስሎ በሚሠራ ላይ በሕግ ክስ ይመሠረትበታል፡፡<br>**የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**<br>ADDIS ZEMEN VOL. LXXXII No. 115- 25/4/2015 (3/1/2023) | |

## INVITATION FOR BID
## IFB No. ECWCT/NCB/PG-76/2015

1. The Ethiopian Construction Works Corporation (ECWC) hereby invites registered eligible bidders for supply of PLY WOOD.
2. Interested Potential Bidders are required to present renewed relevant Trade License for the Ethiopian fiscal year, VAT Registration Certificate, Tax Clearance Certificate and Online Supplier list Registration Certificate together with their offer.
3. Bidding document should be prepared in English language.
4. Interested Potential Bidders obtain a complete set of bidding document from the office of Procurement Department against payment of none refundable fee of Birr 300.00 upon presentation of Trade License renewed for the fiscal year.
5. This invitation of bid is open to all interested potential bidders regardless of their nationality and the bid evaluation and award shall be determined in accordance with the provision indicated in bidding document.
6. The deadline for bid Submission shall be on January 17, 2022, at 02:30 P.M.
7. Bid must be accompanied with a Bid Security of an amount of Birr 100,000.00 ETB (One Hundred thousand) in the form of certified cheque (CPO) or Bank guarantee. Bid Bond in the form of insurance bond or in any other form shall not be accepted.
8. Bids must be delivered or deposited in the Tender Box situated at the office of the Procurement Department on January 17, 2022, at 03:00 P.M. in Ethiopian Construction Works Corporation Procurement Department conference room, in the presence of bidders and/or their representatives who choose to attend.
10. The Ethiopian Construction Works Corporation reserves its rights to reject any or all bids.
11. Bidders may get further information at the following address:

**Ethiopian Construction Works Corporation**
**Address: Gurd shola behind Athletics Federation Building**
**In front of Andinet International school**
**Telephone No.011 8 72 29 58/ 0118 72 30 86/011 896 29 91**
**Telegram Channel-ECWC.BID**

በከሳሽ 1ኛ አቶ ታዲዮስ ፀሃዬ በተከሳሽ 1ኛ ወ/ሮ ሰላም በላቸው ተገኜ መካከል ስላለው የፍቺ ጉዳይ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ ተከሳሽ በፌ/መ/ፍ/ቤት ን/ስ/ላፍቶ ምድብ 7ኛ ቤተሰብ ችሎት እየታየ መሆኑን በዚህ ጋዜጣ ማስታወቂያ ጥሪ አውቀው ለ02/05/2015 ዓ.ም 4፡30 ሰዓት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

በከሳሽ፡- ዶ/ር ሰሚራ ፈረጀ እና በተከሳሾች እነ አቶ አለማየሁ አጀሬ 1ኛ ዶ/ር ሰሚራ ፈረጀ መካከል ስላለው የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ መከሰስዎን አውቀው ለ8/5/2015 ዓ.ም በ3፡30 ሰዓት የተቀጠረ መሆኑን አውቀው በፌ/ከ/ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 5ኛ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡ የማይቀርቡ ቢሆን ጉዳዩት በሌሉበት ታይቶ የሚወሰን መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት**